ኑር የቁርዓን ባንክ

ኢስላማዊ ማኅበር እምስተኛ የምስረታ አመት ልዩ ዕትም መጽሔት ቅጽ I

NUR QURAN BANK ISLAMIC ASSOCIATION



ጉዞ ብርሃን ይዞ

ቁርዓን ለሁሉም



እንደ ቁርዓን ለሸንደ ደረሳ

እንደ ቁርዓን ለሸንደ ደረሳ

1000402052434

0143811100904100

178179616

7114

ለሁሉም ባንክ አጭር ኮድ

+251929591670 +251911285537

0020949710301

1559758700001

1000071140001



ኑረዲን ነስሮ

የኑር ቁርአን ባንክ ኢስላማዊ ማኅበር መስራችና ስራ አስኪሃጅ

بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በኾነው።።

አልሃምዱሊላህ ለዓለማቱ ጌታ ለሆነው ለኃያሉ አላህ (ሱ.ወ) የማያልቅ ምስጋና ይገባው። ኑር የቁርኣ ባንክ ኢስላማዊ ማህበር የቁርኣን ብርሃን ላልደረሰባቸው የምስራቅ አፍሪካ ሃገራት በትጋት ብርሃናማ ጉዞ ለማድረግ አቅዶ ከተነሳ እነሆ አምስት አመታትን አስቆጥሯል። ተቋማችን ከተመሰረተ እለት አንስቶ በኢትዮጵያውያ የገጠር ክፍል ቁርኣን ለማሰራጨት ስናቀና ከመደርደሪያቸው ላይ አንድ ሙስሃፍ አንስተው ለወገኖቻቸው ከማካፈል ፣አህለል ኸይር ሆነው መድረሳና መስጅድ በመገንባት ፣ በገንዘብ ፣በቁሳቁስ አይነት ፣ በሀሳብ ከጎናችን በመቆም አብረውን ለተጓዙ ቤተሰቦችን በሙሉ የላቀ ምስጋናዬ እንዲደርሳችሁ አላህ በመልካም ስራችሁ ሁሉ የማይቋረጥ አጅር እንዲሰፍርላችሁ ዱዓዬ ነው።

ማኅበራችን በመላው ኢትዮጵያ በመዞር ቁርኣን ያልደረሰባቸው አካባቢዎች ሲጓዝ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የቁርኣን ኮፒ በማዳረስ በሉህ ላይ በመሬትና በድንጋይ ላይ እየፃፉ የአላህን ቃል ሲማሩና እስልምናን ለማቅናት በአስቸጋሪ መንገድ የእውቀት ቀንዲል ሲያበሩ የነበሩ ወገኖቻችንን ከወረቀት ጋር እንዲተዋወቁ ለማድረግ ችለናል። በተጨማሪም በዛፍ ጥላ ስር ተጠልለው ይቀሩ የነበሩ ደረሳዎች አህለል ኸይሮችን በማስተባበር መድረሳዎች ገንብተናል ፣ የጁምዓና የጀመዓ ሰላት በጠራራ ፀሐይ ሜዳ ላይ ሲሰግዱ የነበሩ ምእመናን መስጅድ ገንብተን ልባቸው በሃሴት እንዲሞላ የትናንት ሃዘናቸው በሳቅ ተተክቶ ብዙ ታዝበናል ። አልሃምዱሊላህ ውስን ቦታዎች ቢሆንም ይሄን የስኬት እድል በማየታችን አላህን በብዙ እናመሰግነዋለን።

ጉዟችን ሁሉ ገር በገር አይደለም እርስበእርስ ግጭት ጦርነት ባለባቸው ቦታዎች ፣ የአየር ጠባያቸው አስቸጋሪ በሆኑ ቀዬዎች ተጉዘን አማናችንን አድርሰናል። ከእናንተ ከቤተሰቦቻችን ተቀብለን ቁርኣን ልናደርስ ስንኳትን ይዘን የተጓዝነው የቁርኣን ኮፒ ጥቂት ሆኖ ቁርኣን ያልደረሳቸው ደረሳዎች ሲያለቅሱ አብረናቸው አልቅሰናል። ብዙ ትዝብቶች እልህና ቁጭት የሚያጋቡ ሲሆኑ ምነው የቁርኣን ማተሚያ ማሽን እጃችን ላይ በኖረና ደረሳዎቻችን ልባቸው በደስታ ተሞልቶ ቁርኣን ቢቀሩ የሚል ስሜት ውስጣችን ያጭራል። ማኅበራችን ከአህለል ኸይሮች በሚያገኘው ገንዘብ የኸይር ስራውን ለማስኬድ ሲጥር የሚገጥሙን ተግዳሮቶች በመልካም ስራ ላይ ለተሰማራ ሰው ነፍስያን የሚፈታተን ነው። የኢትዮጵያ ገጠራማ ቦታዎች ለመጓዝ የሚያመች የመስክ መኪና ባለመኖሩ የመኪና ኪራይ ወጪ አቅም ከፈቀደው በላይ ሆኖ ጉዟችን ላይ ብዙ ፈተና ደቅኖብናል። በደረስንባቸው ቀየዎች ዒልም ለማቅራት ደፋ ቀና የሚሉ ሸኾች፣ኡስታዞች በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ላይ ሆነው ደረሳዎቻቸውን እንዳይበትኑ ደሞዛቸውን ለመደጎም ኑሯቸውን ለማቅናት ጥረናል። ለተፈናቃዎች አልባሳት ምግብ ቁርኣን ከማድረስ ባሻገር በሰብዓዊ ስራዎች ላይ በየአጋጣሚው ኑር ቁርኣን ባንክ ተሳትፏል።

የቁርኣን ብርሃን ማድረስ ዋናው ግባችን ቢሆንም ሙስሊሙ ማኅበረሰብ የሚገጥሙት ማኅበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊ ቀውሶችን ለመፍታት እንደ ተቋም ከመንግስት ተቋማት እንዲሁም ሁሌም ከጎናችን አብረው የሚጓዙ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤትና የሚዲያ አጋሮቻችን ጋር በመንገዳችን የሚገጥሙንን ተግዳሮቶች ለመፍታት ችለናል ። ወደፊት ላስቀመጥነው ዓላማና ግብ በመላው የምስራቅ አፍሪካ የቁርኣን ብርሃን ለማድረስ ስንቅ ይሆነን ዘንድ አብረውን ለነበሩት ሁሉ በአምስተኛ አመት የጉዟችን ማስታወሻ መሃል ማመስገን ተገቢ ነው።

ኑር ቁርኣን ባንክ ኢስላማዊ ማኅበር ከአንድ ሚሊዮን በላይ የቁርኣን ኮፒዮች ለገጠሩ ክፍል ቢያደርስም ፣ መድረሳዎችና መስጅዶችን ቢያስገነባም ፣ የዘመሙ ሀሪማዎችን ቢያቃናም በዚህ የብርሃ ጉዞ ውስጥ ያልተነኩና ብዙ ጉልበት የሚጠይቁ የቤት ስራዎች እንዳሉበት ተረድቷል። በአዲስ ጉልበት ፣በቤተሰቦቻችን ድጋፍ ያልታዩ እና ድጋፍ የሚፈልጉ ቀየዎች ለመድረስ እንደቀድሞው ሁሉ አንድ ሙስሐፍ ከመደርደሪያ አንስቶ በመስጠት ፣ አህለል ኸይር ሆኖ ለሰደቀቱል ጃሪያ በመረባረብ ፣ እንዲሁም የኑር ቁርኣን ባንክ አባል ሆኖ በመመዝገብ ወገኖቻችንን ወደ ተሻለ የእውቀት ብርሃን ለማሸጋገር አብራችሁን እንድትጓዙ ስንል በትህትና እንጠይቃለን ።

የኑር ቁርአን ባንክ መልዕክት

ውድ የኑር ቁርአን ባንክ መፅሔት አንባቢያን ይህ የማህበራችን አምስተኛ አመት የምስረታ በዓልን ምክነያት በማድረግ የተዘጋጀ ቅጽ 1 መፅሔት ሲሆን ማህበራችን የተቋቋመበት ዋነኛ አለማን ግብ እና ራዕዩን ጨምሮ ባለፉ አምስት አመታት የተሰሩ ስራዎችን ለመግለጽ የተዘጋጀ ነው ።

ማህበራችን ኑር የቁርአን ባንክ በአዲስ አበባ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት በኢስላማዊ ማህበራት አደረጃጀት ዘርፍ ከመመዝገቡ ቀደም ብሎ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ የበጎ አድራጎት ስር ሀጋዊ ፍቃድ በማውጣት ቁርአን የማሰራጨትና ተያያዥ የሆኑ የበጎ አድራጎት ስራዎችን ሲሰራ ቆይቷል ። ሆኖም የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት በአዋጅ ሲቋቋም እና ማህበራትን የማደራጀት ፍቃድ ሲሰጠው ማህበራችን ቀዳሚ በመሆን ምዝገባውን አካሂዶ ሀጋዊ ሰርተፍኬት አግኝቷል ።

ውድ አንባቢያን ማህበራችን በዚህ ዘርፍ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ባለፉት ድፍን አምስት አመታት አንድ ሚሊየን አንድ መቶ ሁለት ሺ (1,102,000) የቁርአን ኮፒዎችን በአላህ ፍቃድ በመላው ኢትዮጵያ ማሰራጨቱን ስናበስር በዚህ የበጎ ተግባር አላማ ላይ ተሳታፊ የነበራችሁ እናንተን ቤተሰቦቻችን ስኬቱ የጋራችን ነውና እንኳን ደስ አላችሁ እያልን በአላህ ስም እጅግ እናመሰግናችኋለን ።

ምን እንኳ ትኩረታችን ቁርአን ማሰራጨት ላይ ቢሆንም ተያያዥ ሆነው የሚሰሩ የመስጂድና የመድረሳ ግንባታዎችን የአልባሳትና የቁሳቁስ ድጋፎችን በተለያዩ የሀገራችን ገጠራማ ቦታዎች በመጓዝ በአላህ እገዛና በእናንተ ቤተሶቻችን ድጋፍ #___ ያህል መስጂድና መድረሳ ተገንብቶ ለፍሬ በመብቃቱ አምስተኛ አመት ምስረታችን በማክበር ላይ ባለንበት ወቅት የጁመአና የጀመአ ሶላቶች እየተሰገደባቸው ፣ መድረሳዎቻችን ውስጥ ደግሞ በሺ የሚቆጠሩ ደረሶች ቁርኣታቸውን እያከናወኑ መሆኑን በመግለፅ በድጋሚ እንኳን ደስ አለን እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት እንወዳለን ።

የማህበራችን ቅጽ 1 መፅሔት በዛሬው ዕለት ለንባብ በቅቷል ። በዚህ የመፅሔት ዝግጅት ወቅት አብረው ለነበሩ ሁሉ ምርጋናችን ይድረሳችሁ እያልን በስራችን ላይ ያላችሁን ማንኛውም ሀሳብ አስተያየት በአክብሮት እንደምንቀበል እየገለፅን በአካል ለመምጣት አዲስ አበባ ፒያሳ ሶማሌ ተራ የገበያ ማዕከል 8ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 830 በተጨማሪም በሁሉም የማህበራዊ ሚዲያ አማራጮች ልትከታተሉን እንደምትችሉ ለማስታወስ እንወዳለን ። መልካም ንባብ ።

መግቢያ

ዓለም በከባድ ድንቁርና ተይዛለች ። ግፍ ተንሰራፍቷል ። ፍትህ ተዛንፏል ። በደል ሀይሏል ። በዳዮች ከዙፋኑ ነግሰዋል ። ተበዳዮች ያለ እንባ አባሽ ቀርተዋል ። አቅመ ደካሞች ተጥለዋል ። የሰው ሃቅ ያለ ከልካይ ይዘረፋል ። ዝምድና ይቆረጣል ። ጉልበት ያለው አቅመ ደካማውን ያጠቃል ። ሴት ልጅ ከነ ሀይወቷ ትቀበራለች ። ይህ ትክክለኛ የዚህ ዓለም መልክ ነው ። ስፍራው የአረቢያ ምድር ቦታው በቂረይሽ ግዛት ስር የነበረችው የመካ ከተማ ወቅቱ ደግሞ 610 ዓ.ል ። በወቅቱ የነበረው የዓለም ስርአት የገዢና ተገዢ መደብ የባሪያና የጌታ ኑሮ ፣ የንጉሥና የሎሌ ድምር ነበረ ። ጥቁሮች እንደ ሰው የማይቆጠሩበት በአሳዳሪ ስር የሰው ልጅ የእኩልነት ቀንበር ተሰብሮ በግፍ ቀኑን የሚገፋበት በቁጭት ሀይወቱን የሚረግምበት አለም ነበረ ።

የታላቁ ነብይ ኢብራሂም ዐ.ሰ ማስታወሻ መልኩን ቀይሯል ግዙፉ ካዕባ ለአንድ አምላክ መገዣ መሆኑ ቀርቶ በ360 ጣኦታት ተከቧል ። በዙሪያውን የጥንቁልና ድር ደርቷል ። የሰው ልጅ በእጇቹ ጠፍጥፎ ለሰራውን ጣዕት በሚሰግድበት በዚያ ከባድ የጅህልና ቀንበር በተሸከመ ማህበረሰብ ውስጥ የዚህን ዓለም የታሪክ ሂደት የሚቀይር አንድ ክስተት ተከሰተ ።

በቂረይሽ ማህበረሰብ ዘንድ እጅግ ተወዳጅ ነው ። እርሱን ፍፁም ያምኑታል ። ለታማኝነቱም ዘወትር ምስክር ናቸው ። በአመለ ሸጋነቱ የታወቀ የስነምግባሩ የመጠቀ በአስተውሎት የረቀቀ ሁሉም በእኩል የሚስማሙበት አንድ ሰው እነሆ ከዓለማቱ ጌታ ስለመላኩ አዋጅ አለ !

በወርሐ ረመዳን 610 ዓ.ል የአለምን ታሪክ የሚቀይር ልዩ ክስተት ተጀመረ ። የጥንታዊው ዘመን አብቅቶ ነበረና አውሮፓ በጨለማው ዘመን መጀመሪያ ላይ ነበረች ። ዳሩ በቂረይሽ ስር የነበረችው የመካ ከተማ ፖለቲካውንና የኢኮኖሚ ስርአቱን በመያዟ ሀያልና የበለፀገች ነበረች ። በዚህ ወቅት ነው ታላቁ ነብይ ሙሐመድ ሰዐወ መለኮታዊ ተልዕኳቸውን ለመፈፀም የአላህን ብቸኛ አምላክነት የእርሳቸውንም መልዕክተኛነት በግልፅ ይፋ አደረጉ ።

ታዲያ ግን የመካ ገዢዎችም ሆነ የቂረይሽ ማህበረሰብ መልክተኛውን በቀላሉ ሊቀበላቸው አልፈቀደም! ይልቁን የእስልምና እምነት ሊያጠፉ ጥቂት የሚሆኑ የመልዕክተኛው ተከታዮቻቸውንም ሊያጠፉ ተነሱ ። የአላህ ጌትነት በአዋጅ እንዳይመሰከር የነብዩም መልዕክተኝነት በይፋ እንዳይወሳ ማዕቀብ ተጣለ ። ግፍ ተንሰራፋ በደል የሙሽሪክች መገለጫ ሆነ ። በመካ ዙሪያ የሚገኙ ሙስሊሞችን አንድ በአንድ እየተከተሉ ማረድ ቤትና ንብረቶቻቸውን በእሳት ማንደድ ጀመሩ ። የመልዕክተኛውና ተከታዮቻቸው ስቃይ በረታ ። መከራ ጠናባቸው ፈተናው እጅጉን የከበደ ሆነ ።

በወቅቱ በተከታዮቻቸው ላይ እየደረሰ ያለ ግፍና በደል እጅጉን ያዘኑት የአላህ መልዕክተኛ የሶሀቦች የህልውና ስጋት ውስጥ መሆን ስለተሰማቸው አንድ መፍትሔ አበጁ! እርሱም በእስልምና ታሪክ የመጀመሪያ የሆነ ስደት ። ጉዞ ወደ አቢሲኒያ ።

የነብዩ ተከታዮች በወቅቱ በክርስቲያኑ መንግስት በንጉስ አስሃማ ስር ወደምትተዳደረው ምድር ሄደው እንዲጠለሉ ታዘዙ ። ታዲያ አል ነጃሺ በመባል የሚታወቁት ንጉስ ፍፁም ፍትሐዊና ታማኝ መሆናቸውን በመመስከር የአላህ መልዕክተኛ ሂዱ አሉ ለተከታዮቻቸው! 'ሂዱ ወደዚያ ፍትሐዊና ሀቀኛ ንጉስ በእርሱ ስር አንድም ሰው የማይበደልበት ለሀቅ ዘብ በቆመ በእውነተኛ ንጉስ ወደምትመራው የፍትህ ምድር' የሐበሾች ሀገር ። አቢሲኒያ ከተማ ።

ዳሩ ከብዙ ተንኮሎች ጀርባ በነብዩ ዱአና በአላህ እርዳታ ታግዘው በፅናት የተፈተኑት የመልዕክተኛው ባልደረቦች በሀብቱ በስልጣኑ እምነቶችን በማቻቻሉና በፍትሐዊነቱ ወደተመሰከረለት የንጉስ አርማህ ግዛት የአክሱም መንግስት የነጃሺ ቤተመንግሥት ደረሱ ።

ኋላ ግን ከቂያቸው በማፈናቀል የበደሉ እንስልምናን ለማጥፋት የሚገድሉ የአረብ መኪንንቶች ስማቸውን ለማደስ የሸሹ ስደተኞችን ለመመለስ እጅ መንሻ ስጦታዎችን በማጉረፍ በአል ነጃሺ ቤተ መንግስት ተገኙ ። ንጉስ ነጃሺም የስደተኞችን ፍላጎት ለመረዳት ጥያቄያቸውን ለመመለስ ንግስና ካጎናፀፋቸው የፍትሕ መድረክ ተሰየሙ! አል ነጃሺ የተላላኪዎችንም ሆነ የሙስሊሞችን የቃል ክርክር ከሰሙ በኋላ ሙስሊሞችን አሳልፌ አንሰጥም ሲሉ በአንድ ቃል ወሰኑ ። መልእክተኞቹን ስጦታቸውን እንዲመልሱ ነገሯቸው ። እናም ሙስሊሞች በግዛቱ እንደፈለጋቸው ለመኖር እና ለማምለክ ነጻ መሆናቸውን አረጋገጡላቸው ። ይህ ታሪካዊ ክስተት በብዙ ምክንያቶች ዛሬም ድረስ በአለም ታሪክ ወደር የለሽ ሆኖ ሰፍሯል።

ብዙም ሳይቆይ ሁለተኛው የስደተኞች ቡድን የነብዩ ሴት ልጅ ሩቂያን ጨምሮ ወደመቶ የሚጠጉ ታላላቅ ሶሀቦች ወደ ሀበሻ ምድር ተመሙ ። የኋላ ኋላም ሙስሊም ስደተኞች ጠንካራ ህብረተሰብ በመገንባት የእስልምና ሀይማኖትን በማስፋፋት ለሀገሪቷና ለመንግስቱ ብልዕግና አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

በወቅቱ የሙስሊም ስደተኞች ወደ ሀበሻ ባደረጉት የስደት ጉዞ በአለም ዙሪያ ላሉ አማኞች መነሳሻ ሆኖ ቀጥሏል ። ይህም በችግር ጊዜ ሰላማዊ መጠጊያ መፈለግና ማግኘት አስፈላጊ መሆኑን አመላክቷል ።

ወደ አቢሲኒያ የተደረገውን የስደት ታሪክ ስናሰላስል የንጉስ አልነጃሺ ትሩፋትና ዘመን የማይሽረው የርህራሄ የመቻቻልና የአብሮነት እሴትን ያስታውሰናል ። የሀበሻ ምድር የኢትዮጵያ ሀገር የሰላም ተምሳሌት ሆና በንጉስ ነጃሺና በሀገሬው ማህበረሰብ የተዋለው ውለታ ዛሬም ድረስ ለእስልምና መስፋፋት ጉልህ አስተዋጽኦ እንደነበረው እንረዳለን ።

ከዚህ ሰፊ ትውፊት ያለው የጉዞ ታሪክ በኋላ የአለም ስርኣት ተቀይሯል ። የመልዕክተኛውን መልዕክት አላህ በጥበቡ ከጫፍ እስከ ጫፍ እንዲዳረስ አድርጎታል እና የአለም ስርኣት ተቀይሯል ። ፍትሕ ሰፍኗል ። ሰዎች የህይወት መንገዳቸውን አግኝተው ጉዟቸው ቀንቷል ። ፈጣሪያችን አላህ በመሐመድ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም በኩል ለአለም ህዝብ ያቀበለው መለኮታዊ መገለጥ የሰዎች ህይወት ቁልፍ መመራያ የሁለት አለም የስኬት ጎዳና ሆኗል ። ቅዱስ ቃሉ ከዚያ ዘመን ጀምሮ እስከ አለም ፍፃሜ መመሪያ ሆኖ ሊያገለግል ሰዎችም አንብበው ይጠቀሙበት ኖረው ይሻገሩበት ዘንድ እነሆ በ114 ምዕራፎች ተሰድሮ ዛሬ ድረስ በሚሊዮኖች በሚቆጠሩ ሰዎች አእምሮ ውስጥ ተቀርፆ በቃል ሲያዜሙት በሁለት ቢሊዮን የአለም ህዝቦች ከፍተው የሚያነቡት ተአምራዊው ቅዱስ ቁርኣን መመሪያ ሆኖ ይኖራል ። ታዲያ በመግቢያች የገለፅነው ያቺ ለእስልምና መስፋፋት ጉልህ ድርሻ ያላት ድንቅ ሀገር ከመዲና ከተማ ቀድማ በአለም ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የእስልምና እምነትን ተቀብላ ያስተናገደች ውቢ የሐበሻ ምድር ዛሬ ድረስ መልዕክተኛው ይዘውት የመጡትን መለኮታዊ መገለጥ በጥበብ የተሞላው አስገራሚው የአላህ ቃል የህይወት መመሪያ የሆነው ቅዱስ ቁርኣን (ሙስሀፍ) ማግኘት ተስኗት እጅግ በሚያስገርም መልኩ ከ1500 ዓመታት በኋላም መልዕክቱን ጣውላ ላይ በመቅረጽ የሚማሩ በሺዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎች ያሏት ምስኪን ሀገር ሆናለች ።

የጉዞ ማስታወሻ

ከ ሀሸም ሙዘይን

ህዳር 8 ቀን 2016 ዓ.ል ። የአዲስ አበባን ሞቃት አየር ለቀን ቀዝቃዛውን የባሌ ተራራ ንፋስ ማጣጣም ከጀመርን 19 ሰአታት አልፈዋል ። ሹፌራችን ብርቱ ነው! ያለ ማቋረጥ ይነዳል ።

ለዘመናት እልፎች በአሀያ እንጂ የማይጓዙበት : ምናልባት ጥቂቶች ብቻ በሞተር ሳይክል የሚመላለሱባት : ባለንበት ክፍለ ዘመን እንኳ ለመኪና ጉዞ እጅግ የከበደ መንገድ አቅፋ የያዘችውና 'ትንሿ የሙስሊሞች መንደር' በሚል ተቀፅላ ስም ወደ ምትጠራው የኦጋዴን ድንበር ጎረቤት 'ሰዌና' ከተማ ።

'ጉዞ ብርሃን ይዞ' ሲል የሰማይ ቤቱን ደብዳቤ በምድር ለማሰራጨት ከአዲስ አበባ የተነሳው የኑር ቁርኣን ባንክ የጉዞ ልዑክ እነሆ ከ7ሺ በላይ ሙስሀፎችን በጁዝ ለያይቶ በመጠን አደራጅቶ ከ 700 ኪ.ሜ በላይ ተጉዞ ነበር ምስራቅ ባሌ ዞን ሶማሌ ድንበር አቅራቢያ ወደምትገኘው ሰዌና ወረዳ ያቀናነው ።

እርግጥ የመንገዱ 1/3ኛ ከባድ ፒስታ ከመሆኑ ጋር የአየር ሙቀቱ መቀያየርና የመዳረሻችን መራቅ ጉዞውን ከባድ አድርጎት ነበር ። ዳሩ ወንድምን በመዘየርና ቁርኣንን በማሰራጨት ውስጥ የሚገኝ ሀሴትን መናፈቅ ለድካማችን መድሀኒት ሆኖ ነበረና ማምሻውን በምድረ አሸዋ የተሞላችው ሞቃቷ ከተማ ሰዌና ደረስን ።

አቀባበሉ ለጉድ ነበር ። እነርሱ ቁርኣን ይዞ የመጣን እንግዳ ይቅርና የመሸበትን መንገደኛ እንኳ እግር አጥበው በእርጎ አጥገበው ማሳደር ባህላቸው ነው ። ታዲያ እኒያ ነጭ ፂማቸውን በቀይ ሂና ያስዋቡ በሻሻ አዛውንቶች ለእኛም ቤታቸውን አሙቀው አልጋቸውን ለቀው ነበር በክብር ከእልፍኛቸው የጋበዙን ።

እኛን ፣ የልጅ ልጆቻቸው የምንሆን አፍላዎችን አክብረው ከፊታቸው አስቀምጠው በጨዋ ደንብ ሹራ (ምክክር) ጀመሩ ። ልሳናቸው ለጣፋጭ ኦሮምኛ እንጂ ለአማርኛ አልገራምና በአስተርጓሚ እንኳን ደህና መጣችሁ ሲሉ ስለ ባህላቸው አኗኗርና ቀዬአቸው ጥቂት ነገሩን ።

ለዲን የሚታትሩ ለዱኒያ ግድ የሌላቸው ፣ ዘያሪ ወንድም የናፈቁ በሚልም ጥግ ድረስ የበቁ ተናንሰው የሚያነግሱ ምስኪኖች ሆነው እንጂ አላገኘናቸውም ። እርግጥ ነው ላለፉት 7 አመታት የሰማይ ዝናብ ከድቷቸው በድርቅ የተጎዱ ፣ በከባዱ በረሃ ሙቀት የነደዱ ቢሆንም ከዱንያ ችግራቸው በላይ የሚያሳስባቸው የልጆቻቸው ቁርኣን ያለማግኘት ነበር ። ዛሬ ድረስ ብዙዎች በ'ሉህ' (እንጨት ላይ ፅፈው) ሲቀሩ ጥቂቶች ብቻ በ1 አሮጌ ቁርኣን ለ6 ተፈራርቀው ሲቀሩ መኖራቸው ነው የነርሱ ህመም ።

ሌላኛው ችግራቸው መድረሳ ነው ። በሺዎች የሚቆጠሩ ደረሶችን አቅፈው የዛፍን ጥላን እንደ መሰብሰቢያ ፣ የእሳት ብርሃንን እንደ መሞቂያ ፣ ከሰልን ደግሞ እንደ መክተቢያ በመጠቀም ያለ መጠለያ ልጆቻቸውን ያስቀራሉ ። ይሄ በርካታ አመታትን የተሻገረ የቂርኣት ሂደት ነው ። ታዲያ በዚህ አያያዝ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሮ ሀፊዞችና በሺዎች የሚቆጠሩ ቃሪዎችን አፍርተዋል ። ይህ ከነገሩን እውነት ጥቂቱ ነው ። ታዲያ ምሽቱንና መድከማችንን ያስተዋሉ ካዲሞች 'በሉ የእንግዳ ወግ ነውና ምን እንኳ ልጅ ብትሆኑም ለአባቶቻችሁ ዱአ አድርጉ' ሲሉ ነጫን ፍየል አምጥተው እፊታችን ለእርድ አቆሟት ። የእውነት ደነገጥን ።

በዚህ መንገድ ነበር ከሰዌና ወረዳ የእምነት ወንድሞቻችን ጋር የተዋወቅነው ። ማታ በወጣው ኘሮግራም መሰረት ጠዋቱን ከተማ ውስጥ ወደሚገኘው ትልቅ መስጂድ በጋራ አቀናን ። በሺ የሚቆጠሩ ደረሶች ግቢውን ሞልተው በተክቢራ ተቀበሉን ። ከተረነገን በላይ ቦታው ላይ ቆመን ያየነው ብዙ ጉድ ነበር ።

ቁርኣን የሚያውቁት በአቅሪአው እጅ ላይ ብቻ ነበር ። ታዳጊውቹ ጣውላቸውን ተሸክመው እንደቆሙ ከመኪና የሚወርደውን ቁርኣን ባለማመን ስሜት እያዩ ሲደሰቱ በዓይናችን ተመለከትን ። አላህ ብዙ ባሮች አሉት ። ቃሉን ለማንበብ የሚጓጉ ሙስሀፉን ለመዳሰስ የሚሽቀዳደሙ የቁርኣን ትውልዶች ።

ፈተናው የጀመረው እዚህ ላይ ነው ። ይዘን የመጣነው ቁርኣን ከጠበቀን ደረሳ ብዛት አንፃር እጅግ አናሳ ነበር ። የልጆቹ ጉጉት የኡስታዞቻቸው ደስታ የእኛን ልብ ፈተነው ። የኋላ ኋላ የመጣውን ቁርኣን ለግማሾቹ ሰጥተን ለቀሪዎቹ ግን በአላህ ፍቃድ ተጨማሪ ቁርኣን ይዘን እንደምንመጣ ቃል በመግባት ልባቸውን ጠግነን ከቦታው ለቀን ወጣን ።

ወደ አዲስ አበባ እየተመለስን ነው ። ዳሩ አካላችን እንጂ የሁላችንም መንፈስ ልጆቹ ጋር ቀርቷል ። በመኪናችን ዝምታ ሰፍኗል ። ሁሉም በሀሳብ ባህር እየተብከነከነ ነው ። መቼ ? እንዴት ? ይሁን የእኒህን ታዳጊዎች ፍላጎት የምንፈፅመው ? ቃላችንን አክብረን ዳግም እነርሱ ጋር ለመመለስ እጅግ ብዙ ቁርኣኖች ያስፈልጋሉ ። ምን ብለን ማህበረሰባችንን እናነሳሳ ? በምን አይነት ቻሌንጅ ቀሪ ቁርኣኖችን እንሰብስብ ?! የጉዞ ልዑኩ ጭንቀት ሀሳብ ነበር ።

አልሐምዱሊላህ አሁን አዲስ አበባ ደርሰናል ። መንፈሳችን ግን አሁንም ሰዌና ወረዳ እዚያች መስጂድ ውስጥ ቀርቷል ።

ሲዳማ

ሲዳማ ክልል ተገኝተናል ። ከሀዋሳ ከተማ 35 ኪ.ሜ ርቀት ተጉዘን በኦሮሚያና በሲዳማ ክልል ድንበር መሐል ወደምትገኝ አንዲት ገጠራማ ቦታ ። እጅግ ለቁርኣን ፍቅር ያላቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ አፍላ ደረሶች ግቢውን ሞልተው በሞቀ ተክቢራ አቀባበል አደረጉልን ። እኒህ ለአመታት የዘለቀ የቁርኣን አቅርቦት ጥያቄ ሲያደርጉ የቆዩ የአካባቢው ነዋሪዎች ለመጀመሪያ ግዜ የቁርኣን ስጦታ ሊቀበሉ በመሆኑ ደስታቸው ወደር አልባ ጉጉታቸውም የላቀ ነበር ። ከፊታቸው ሞልቶ የሚፈሰው ደስታ ተጋብቶብናል ።







ነገሩ የኢድ በዓል እንጂ የእንግዳ አቀባበል ዝግጅት አይመስልም ነበር ። ኋላ ስንረዳ አካባቢ በታሪኩ የብዙ ሙሉሊም ነዋሪዎች የነበረ ፡ ሸሪዓ ከፍ ብሎ የሚንፀባረቅበት ማህበራዊ ትስስሩ ጉርብትናው ጠቅላላ የአኗኗር ዘዬአቸው የሙስሊም ባህል የነበረ ሲሆን ከ10 አመታት ወዲህ ግን ነገሩ ሁሉ ግራ ሆኖ ረሀቡ ሲበረታ ሰዎች ዲንን ከመማር ይልቅ የእለት ምግብ ፍለጋ ሲራወጡ ታዳጊዎች ከመድረሳ አዋቂዎች ከጀመአ ቀስ በቀስ ሲገለሉ ለዘመናት የአካባቢውን ማህበረሰብ ለማክፈር ሲቋምጡ ለኖሩ ባለ ተልዕኮዎች አጋጣሚው ሰርግና ምላሽ ሆነላቸው ። ከፊት የእርዳታ ታፔላ ለጥፈው ከጀርባ ሀይማኖት የማስቀየር ስራ በመስራት ችግርና መከራን እንደ መልካም አጋጣሚ ተጠቅመው እኒያ ሁሉ የአካባቢው ነዋሪዎችን አጠመዷቸው ።

ታዲያ ረሀብን ተቋቁመው ችግርና መከራን ችለው የቆዩ ጥቂት አባዎራዎች እምነታቸውን በማጠንከር ልጆቻቸውን በማስቀራት ከአካባቢው የዲን ብርሃን እንዳይጠፋ የቻሉትን ሁሉ ሲያደርጉ ቆይተዋልና ዛሬ ላይ የሚጎበኛቸው እንግዳ ከምድር ስጦታዎች ሁሉ የላቀውን ስጦታ 'ቅዱስ ቁርኣን' ይዞላቸው ሲመጣ እንዴት ላይደሰቱ እንዴት ላያነቡ እንዴት ቀኑን ኢድ ላያስመስሉ ይቻላቸዋል?! አጂብ ነበር አቀባበሉ ።

የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉልን የመስጂዱ ኢማም እና የተማሪዎቹ ኡስታዞች ነበሩ ። ታዲያ የዘመናት ብሶታቸውን የከፋ ኑሯቸውን ወንድም ነንና አጋሩን ። 'ልጆቻችን ከፍረው አለቁ በቁማችን እየሞትን ነውና ለአላህ ስትሉ ታደጉልን' ነበር ቋንቋቸው ። በእንባ ተሞልተው ይህን ሲሉን ሀዘን ተናንቆናል ። ምን ማድረግ እንችላለን ? ስንል አባቶችን ጠየቅን ። እነርሱም ይህን ከመመለሳችን በፊት በዚህ ሞቃት ቦታ እንዴት ልጆቻችን እየተማሩ እንዳሉ ተመልከቱ ሲሉ ግቢውን ያስጎበኙን ጀመር ።

ያ በእልፍ ህፃናት የሞላው የመስጂዱ ቅጥር ግቢ ከወደ ጀርባው አንዲት ለመፍረስ ቀናትን የምትጠብቅ ምሰሶ የከዳት ጭቃና አፈር የራቃት ጠባብ ክፍል አሳዩን ። ከጎን በምስሉ የምትመለከቱት ይህ መድረሳ ለበርካታ ዘመናት ደካማ የኑሮ መሰረት ካላቸው የአካባቢው ነዋሪዎች በተገኘች ጥቂት ፍራንክ እንደነገሩ ተገንብታ ልጆቻቸውን በአክፍሮት ሃይላት ላለማስነጠቅ በዲን ለመጠበቅ ሲሉ እንዲቀሩ ያደረጉባት ታሪካዊ መድረሳ ናት ።

በዚህ አሳዛኝ ገጠመኝ የተሞላ የሲዳማ ጉዞ ለአካባቢው ማህበረሰብ ያመጣየውን ቁርኣን ሰጥተን በምትኩ ከበድ ያለ አማና ተቀብለን ነበር የተመለስነው ። እነዚህን ጀግና አባቶች ምርጥ የኢስላም ልጆች የእውነት እስልምና ያስተሳሰረን ወንድሞች አሉን የሚል የብርታት ስሜት እንዲሰማቸው ማድረግ እምነታዊ ግዴታችን ተቆማዊ አላማችንም ነበር ።

ታዲያ ጉዳዩን ለእናንተ ለቤተሰብቻችን በማቅረብ በቀናት ውስጥ በጎ ምላሽ በዛው ፍጥነት ቀድሞ ደራሽ በመሆን ለእኒህ ጠንካራ ወንድምና እህቶች ትልቅ የደስታ ብስራት ዘላቂ የዲን መብራት ይሆን ዘንድ ቃላችንን በማክበር አማናችሁን በመወጣት ከታች በምስሉ ላይ የምትመለከቱትን ዘመናዊ ባለ 3 ክፍል መድረሳ ገንብተን በደማቅ ሁኔታ በማስመረቅ ለአካባቢው አባቶች አስረክበን የሞቀ ዱአቸውን ተቀብለናል ።

የአክሱም ድምፃችን

ከ ሀሽም ሙዘይን

አክሱም የጥንታዊ ሥልጣኔ እና የሃይማኖቶች መገኛ ስትሆን፣ የእስልምና ታሪክም በዚች ምድር ልዩ ቦታ ይዟል። ከጥንት ዘመናት ጀምሮ አክሱም ታላቅ ከተማ ነበረች። የከበሩ ነገሥታት፣ የከበሩ ቤተ መንግሥቶች፣ እና ከሩቅ አገር የሚመጡ ነጋዴዎች የከተማዋን ግርማ ሞገስ ያሳዩ ነበር ። እስልምና በታላቁ ነብይ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አማካኝነት በመለኮታዊ ብርሃን ታጅቦ በዓረቢያ ምድር ሲገለጥ ነገሩ በአረቦች (በቁረይሾች) ዘንድ ቁጣን ያስነሳና በመልክተኛው ተከታዮች ዘንድ ቅጣትና መከራን ያመጣ ሆኖ ነበር ።

አንድ ቀን፣ ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በተከታዮቻቸው ላይ የደረሰውን ግፍና በደል ለማስታገስ ሲሉ፣ “ወደ አቢሲኒያ ሂዱ፣ በእርግጥም እዚያ ፍትሃዊ ንጉሥ አለ፣ ማንም የማይበደልበት” አሏቸው። እናም፣ ትንሽ የሙስሊሞች ስብስብ አደጋን ተጋፍጠው ቀይ ባህርን ተሻግረው ወደ አክሱም ምድር አመሩ።

የአክሱም ንጉሥ ነጃሺ (አስሐማ ኢብኑ አብጀር) በእውነትም ጻድቅ ንጉሥ ነበር። የሙስሊሞችን ታሪክ አዳመጠ፣ የቁርኣንን አንቀጾች ሰማ፣ እናም በእነሱ ላይ ለደረሰው ግፍ አዘነ። ከሌላኛው ወገን የመጡት የቁረይሽ መልዕክተኞች ሙስሊሞችን አስረክቦ እንዲመልሳቸው ቢጠይቁትም፣ ንጉሡ “እነዚህን ሰዎች አልከዳቸውም!” ብሎ በቆራጥነት መለሰ። ንጉሥ ነጃሺ ለሙስሊሞቹ መጠለያና ጥበቃ ሰጣቸው። ይህ የአክሱም ሙስሊሞች መምጣት፣ የመጀመሪያው የእስልምና ስደት ተብሎ ይታወቃል።

በአክሱም ምድር፣ ሙስሊሞች በሰላም መኖር ጀመሩ። ከመካከለኛው ምስራቅ ባህልና ሃይማኖት የተለየ ቢሆንም፣ የአክሱም ህዝብ በእንግድነት ተቀበላቸው። ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ጎን ለጎን ኖሩ። እርስ በእርሳቸው ተማማሩ፣ ተከባበሩ። መስጂዶች ከቤተ ክርስቲያኖች አጠገብ ተመሰረቱ። ሙስሊሞች የንግድ ሥራቸውን ቀጠሉ፣ ዕውቀታቸውን አካፈሉ። ንጉሥ ነጃሺ በህይወት ዘመኑ ሁሉ ለሙስሊሞች ታማኝ ወዳጅ ሆኖ ቆየ። ነቢዩ መሐመድም የነጃሺን ሞት ሲሰሙ የጋይብ ሶላት (ለሩቅ ለሞተ ሰው የሚሰገድ ሶላት) ሰግደውለታል።

ይህ የአክሱም የቀደመ ግዜ የፍትህ የእኩልነትና በአካታችነት የጠበቀ ወግና ባህል ዛሬ ላይ ተረስቶ አክሱም ከተማ ውስጥ ተወልደው ያደጉ ሙስሊሞች በማንነታቸው የተገፉ በእምነታቸው ምክኒያት የተበደሉ ሆነው እናገኛቸዋለን ። አክሱም ከተማ ውስጥ ተወልዶ ከማደግ ጎርምሶ ጎጆ እስከመቀለስ የደረሱ የፍትሕ ሚዛን ጎድሎባቸው የእኩልነት ጥያቄ ሲያነሱ እየተገፉ ሲከፋም እየተጨቆኑ በትግል ህይወታቸውን ይገፋሉ ። ታዳጊ ልጆቻቸው በተደራጀ መልኩ ቁርኣን እንዳይቀሩ መድረሳ እንዳይኖራቸው ተደርገዋል ። የሁላችንም የቅርብ ግዜ ትዝታ የሆነው የ2018 ዓ.ል የ12ተኛ ክፍል ሙስሊም ተማሪዎች የእምነት ግዴታ የሆነውን ሂጃብ ለብሰው እንዳይማሩ ፈተናም እንዳይቀመጡ ታግደዋል ። በከተማ ደረጃ የሚታወቅ የሙሴሊሞች የአምልኮ ቤት (መስጂድ) እንዳይገነባ ሚናራ እንዳይታይና የአዛን ድምፅ እንዳይሰማ ከተደረገ ዘመናት ተቆጥረዋል ። ያም ሆኖ ግን በፈተና የታጀበ በትግልና ትዕግስት ይፀናልና የከተማው ሙስሊም ነዋሪዎች በእምነታቸው ጠንካራ በመንፈሳቸው ሃያል ናቸው ። ለበርካታ ዘመናት የግለሰብ ቤት ተከራይተው የጀመአና ጁመዓ ሰላታቸውን እየሰገዱ በጠባብ ክፍሎች ልጆቻቸውን ቁርኣንና ሀዲስ እያስተማሩ ዛሬ ድረስ



አርጅተው ህይወታቸው ያለፈ ሙስሊሞች የጋራ መቀበሪያ ስፍራ ተነፍገው ከከተማው ርቀው ነው ዶሪሃቸው (የመቃብር ስፍራቸው) የሚገኘዉ ። ይህ የተኖረ እውነት በወሬ ያደመጥነው በፅሁፍ ያነበብነው አይደለም ። ይልቁን ቦታው ላይ ተገኝተን በዓይናችን ተመልክተን ያረጋገጥነው ሀቅ ነው ። ይሄ የአክሱም ጉዟችን እውነተኛ ታሪክ ነው ።

ከአክሱም ከተማ ሙስሊም ነዋሪዎች የቀረበ ተደጋጋሚ የቁርኣን አቅርቦት ጥያቄ ነበር ። ታዲያ በድርጅታችን ውስጥ ከቀረቡ ጥያቄዎች የምላሽ ወረፋቸው ከደረሱት ውስጥ አንዱ አክሱም ነበር ።

ወንድማችን ኑር ታጁ የጉዳዩ አስፈፃሚ ሆኖ በከተማው አባቶችና በአክሱም ከተማ እስልምና ጉዳዮች ሃላፊ (አመራሮች) ምርጫ መሰረት ለእኛ ተመድቦ የጉዞ ልዑኩን ለመካደም ተዘጋጅቷል ። የአክሱም ከተማ የደረስነው ምሽት 12:00 ሰአት ነበር ። አዳሩን ስለ ከተማው ሁኔታ ማብራሪያ አደረጉልን ። በወቅቱ በፀጥታ ጉዳይ በከተማው ብዙ ጥብቅ ክትትሎች እየተደረገ ስለነበረ እንቅስቃሴዎች በገደብና በተጠና መልኩ እንዲከናወኑ ፣ ከተማው ውስጥ ያሉ የኪራይ መስጂዶችን ለመዘየርና ለታዳጊዎቹ የቁርኣን ስጦታ ለማበርከት እቅድ በማውጣት ለጠዋት ቀጠሮ በመያዝ አዳሩን ተለያየን ።

ጠዋቱ ሞቃት ከመሆኑ ጋር ከወጣቶቹ እኩል አዛውንቶች በሳይክል አስፓልቱን ሞልተው መመልከታችን አስገርሞናል ። እኒያ በእምነት ፅናት የታወቁ በታጋሽነት የበቁ ተምሳሌት ከሆኑ የአክሱም አባቶች ጋር ተገናኘን ። የወንድም ዚያራ በማግኘታቸው ደስታቸው ወደር አልነበረውም ። በዛኑ ቀን ልዑኩ በሁለት መኪናዎች በመከፈል ከተማው ውስጥ ያሉ የኪራይ መስጂዶችን መጎብኘት ጀመርን ። ይህን አሳዛኝ ክስተት ለእምነት የተከፈለ መስዋዕትነት በዓይናችን ተመልክተን ማስቀረቱ በደል መስሎ ስለታየን በያዝነው ካሜራ የአክሱም ሙስሊሞች ድምፅ ለማሰማት ምስሎችን በመረጃ በደሎችን በማስረጃ ለመላው አለም ለማስመልከት ደፈርን ። ውድ አንባቢያን ይህ ታሪክ በወርሐ ረመዳን በሚንበር ቴሌቪዥን መስኮት ለህዝበ ሙስሊሙ እንዲታይ በማድረግ ቁርኣን ከማሰራጨት ባለፈ የአካባቢው ነዋሪዎች ድምፅ በመሆን በአላህ ፍቃድ አሻራችንን አኑረናል ። ይህንን ዝግጅት አድርጅታችን የዩቲዩብ መስኮት ለታሪክ አስቀምጠናል ።

በዛ ታሪካዊ የዚያራ ቀን ያመጣናቸውን ቁርኣኖች በታዳጊዎች እጅ ላይ በማስቀመጥ በአማኞች ልብ ላይ ደስታ ጭረን አማናችሁን አድርሰናል ። ታዲያ ግን የአክሱም ሙስሊሞች በእምነታቸው ምክነያት እየደረሰባቸው ስላለው መገፋት በዓይናችን ተመልክተን ስናበቃ ድምፅ በመሆን ቢያንስ እነዚህ የኪራይ መስጂዶች አላህ ፈቅዶና ታሪክ ተቀይሮ ከተማውንም የከተማው ነዋሪዎችንም የሚመጥን መስጂድ እስኪገነባ ድረስ እነዚህ በወርሃዊ ኪራይነት ከግለሰቦች የተከራዩዎቸው መኖሪያ ቤቶችን የቤት ኪራይ በመክፈል ከአመት አመት ያለ ችግር ይሰግዱና ቁርኣን ይቀሩ ዘንድ የበኩላችንን እንድንወጣ ዛሬም በአላህ ስም እናንተ ውድ አንባቢያንን እንጠይቃለን ።

በመጨረሻም በአክሱም ከተማ ውስጥ በነበረን ጉብኝት እጅግ በሚያስደስት መልኩ ያልጠበቅነውን ታሪክ ያየንበት የሰማንበት ዛሬም ድረስ አጂብ እያልን እንድንገረም ሰበብ ወደ ሆነን ክስተት አመራን ። እዛው አክሱም ከተማ ውስጥ ከኪራይ መስጂዶች ውጪ ለቁጥር አንድ ሆና በብቸኛነት ለሙስሊሙ ማህበረሰብ እፎይታ በመሆን በጀመአ ሶላት የሚሰገድበትና በተጠና መልኩ ታዳጊዎች ቂርኣት የሚቀሩበት ዘመናዊ መስጂድና መድረሳ ተመለከትን ። በአንዲት አስገራሚ ግለሰብ ሁለንተናዊ አቅም የተገነባ ።

በትግራይ ክልል አክሱም ከተማ 05 ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት ወ/ሮ ሸምሲያ ሸህ ሷሊህ በቅፅል ስማቸው (አብሻይ) ። እኒህን እናትን ለመዘየር የታደለው የጉዞ ልዑካችን ከተማ ውስጥ ባለው እንቅስቃሴ የተሰበረው ልባችን የተጠገነበት የመቻልን አቅም ያየንበት ለነገ ለአክሱም ሙስሊም ነዋሪዎች ተስፋ የሰነቅንበት አስደሳች አጋጣሚ ነበር ።

ከጎን በምስል የምትመለከቱት መስጂድ እኒህ እናት በሳዑዲ አረቢያ ኑሯቸው ያገኟትን ገንዘብ በማጠራቀምና ወዳጆቻቸውን በማስተባበር ተወልደው ላደጉባት ከተማ ብርሃን የፈነጠቁበት ታሪካቸውን በወርቃማ ብዕር ያፃፉበት ትልቅ ስራ ነው ። አይቻልም የሚል መንፈስን በይቻላል የተተካበት የአንድ ሰው ጥልቅ ሀሳብ ትውልድን ለመቀየር የሚችል ሃይል እንዳለው የተገነዘብንበት ልዩ ክስተት የእማማ ሸምሲያ የሀሳብ ጉልበትና ትውልድን የመቀየር ኒያ የተመለከትንበት የዚያራ ቆይታ ነበር።

አክሱም ተስፋ አላት ። አክሱም ልጆች አሏት ። አክሱም ወጣቶች አሏት ። አክሱም ጠንካራ አባቶች አክሱም ድንቅ እናቶች አሏት ። የጉዞ ልዑኩ በወቅቱ የተሰማውን የተደበላለቀ ስሜት ለታሪክ በካሜራ በማስቀረት ለአለም አሳይቷል ። ውድ አንባቢያን እኛ ሙስሊሞች ዘር የማይለያየን ቋንቋ የማይገድበን ርቀት ማይወስነን በዘልአለማዊ የላኢላሃ ኢለሏህ ገመድ የተሳሰርን በመሆናችን ፣ ከቅርቢቷ አለም ዱንያ ይልቅ ዘልአለማዊ አኼራ የሚያጓጓን የነፍስ ትስስር ያለን በመሆናችን ነውና የአንዱ በደል የሚሰማን የአንዱ ጭቆና የሚያመን ነን ። ታዲያ የአይንና ቅንድብ ያህል ተቀራርበን ነገር ግን እርስ በእርስ ያለመዘያየራችን በፈጠረው ክፍተት አንድ ሀገር እየተጋራን ድምፃቸውን ያልሰማን ችግራቸውን ያልተረዳን የአክሱም ሙስሊሞች የኛን ድምፅና ድጋፍ አይዟችሁ ባይነትና እገዛ ይፈልጋሉና በምንችለው ሁሉ አለን እንድልላቸውና በመከራ ውስጥ ፀንተው ተስፋን ለፈነጠቁ እንደነ ወ/ሮ ሸምሲያ (አብሻይ) አይነቶችን ልናበረታቸው ግድ ይለናል ።

የኑር ቁርኣን ባንክ የጉዞ ልዑክ በአክሱም ቆይታው ከሞላ ጎደል በወፍ በረር ቅኝት ይህን ይመስል ነበር ። አላህ ለተጨቆኑ ፍትህን ለተበደሉ ድጋፍን ለተጨነቁ ሁሉ እገዛን እንዲሰጥ እየተማፀንን የአክሱም ሙስሊሞችን ለመጎብኘት ለማገዝና ድጋፍ ለማድረግ በፈለጋችሁ ግዜ ሁሉ ተቋማችን በፍፁም ደስታና በሞሉ ጊዜ ተባባሪነት አብረናችሁ እንደምንሆን እንገልፃለን ።

አደይ መቐሌ

ከ ሀሸም ሙዘይን

የ1445ኛ ዓ.ሂ የረመዷን ፆም ወቅት ነበር ። ማክሰኞ ቀን 7:10 የዝሁር ሶላታችንን አየር መንገድ ውስጥ ከሚገኝ የፀሎት ቦታ (መስጂድ) ሰግደን ወደ አውሮፕላን መሳፈሪያ ለማለፍ አዳራሽ ውስጥ ገባን ። ከወትሮ በተለየ አዳራሹ በሰዎች ብዛት ተጨናንቋል ። እንዲያም ሆኖ ግን ከጩኸት ይልቅ ዝምታ ነግሷል ። የአብዛኞቹ ተጓዦች ፊት ላይ ሀዘን ይነበባል ። ከፊሎቹ ፊት ላይ ደስታ እና ጉጉት ፍርሃት እና ናፍቆት ይነበባል ። የኑር ቁርአን ባንክ የጉዞ ልዑካን በተመሳሳይ ግራ የሚያጋባ ስሜት ውስጥ ሆነን የበረራ ሰአታችንን እየተጠባበቅን ነው ። በነገራችን ላይ ይህ ጉዞ ከሁለት አስከፊ የጦርነት አመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ መቀሌ ከተማ የሚደረግ በረራ ነው ።

በወንበር ቁጥራችን መሰረት ተቀምጠናል ። ከእኛ ጎን ለጎን የተቀመጠ አንድ ወጣት አውሮፕላን ውስጥ ከገባንበት ደቂቃ ጀምሮ ያለማቋረጥ ያለቅሳል ። ይቆማል መልሶ ይቀመጣል ። ኋላ ኘሌኑ ተነስቶ ጉዞ ሲጀመር ወጣቱን ለማውራት ሞክረናል ። ያ ሚስኪን ከሁለት አመት በኋላ በጦርነቱ ምክንያት የተለዩ ወላጅ እናትና አንድ እህቱን ለማግኘት ጓግቷል ። በምን ሁኔታ አገኛቸው ይሁን ሲል ይብከነከናል ። ይህ የሙሉ ተሳፋሪዎች ስሜት ነበር ። እኛም የናፈቁን ወንድሞችን ለመዘየር ስጋ ሳይሆን እስልምና ያዛመደን ወገኖችን ለማግኘት ጓግተናል ።

ወደ መቀሌ ከተማ ለመጓዝ ቀጠሮ የያዝነው ከጦርነቱ በፊት የመቀሌ ከተማ ወጣቶች የኡሙ አይመን መረዳጃ ጀመአዎች ተደጋጋሚ የቁርአን አቅርቦት ጥያቄ ደጅ ስለጠኑ እና በትግራይ ገጠራማ ቦታዎች ያሉ ደረሶች ቁርአን አጥተው እንጨት ላይ ፅፈው እየቀሩ እንደሆነ ስለተረዳን ነበር ይህን ቀጠሮ የያዝነው ። ታዲያ እንደ ሀገር የተፈጠሩ ችግሮች ከእነዚህ የአላህ ቃል ከናፈቁ ደረሶች አራርቆን ቆየና ሰላም በሰፈነ ማግስት የመጀመሪያ ጉዟችን ወደ መቀሌ ከተማ ሆነ ።

'ክቡራትና ክቡራን መንገደኞቻችን ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ መቀሌ ከተማ አሉላ አባነጋ አየር ማረፊያ እንደርሳለን' ። የሚል ድምፅ ከሀሳባችን አባነነን ። ከተማዋን ከላይ ወደ ታች ቁልቁል ተመለከትናት ። ከአንድ ቦታ ያለማቋረጥ የሚታይ ጭስ የተሳፋሪዎችን ትኩረት ስቧል ። ምንድን ነው ይሄ ጭስ የሚሉ ጥያቄዎች ሲበዙ ከተሳፋሪዎች አንዱ "አትረበሹ ይሄ የመሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ጭስ ነው" ብሎ አረጋጋን ። የከተማው የላይ ገፅታ ፍፁም 2 አመት የጦርነት ቀጠና ሆና የከረመች አትመልስም ። በአግራሞት ማውጋታችንን ቀጠልን ። 9:20 ኘሌኑ በሰላም እንዳረፈ ተሳፋሪው በደስታ አጨበጨበ! ለአመታት የተነፋፈቁ ወዳጆች ሲገናኙ ህፃናት ከወላጆቻቸው ባል ከሚስቱ ወንድም ከእህቱ ያ አስከፊ ጊዜ አልፎ በሰላም ተገናኝተው በደስታ ሲላቀሱ ተመለከትን ።

ኡሙ አይመን መረዳጃ ከተቋቋመ (7) አመታትን ያስቆጠረ ሲሆን መቀመጫውን መቀሌ ላይ አድርጎ በመላው የትግራይ ከተሞች እና የገጠሩ ክፍል የኸይር ስራዎችን የሚሰራ ተቋም ነው ። የተቋሙ አመራሮች ደስ በሚያሰኝ የክብር አቀባበል ተቀብለውን አየር መንገዱን ለቀን ወጣን ። በቀኝ በኩል ሰሜን እዝን በግራ በኩል አየር ሀይልን አልፈን መከላከያ ኮሌጅ መቀሌ ዩንቨርሲቲን (አርዲ) አቋርጠን ከወንድሞች ጋር ስላለፈው ጊዜ በትዝታ እያወጋን ወደ መሐል ከተማ ተጓዝን ።

ከተማው ፍፁም የጦርነት ጠባሳ ያለበት አይመስልም ። የሞቀ የንግድ ገበያ የትራፊክ መጨናነቅና የዘነጡ ወጣቶች አዲስ አበባን የሚስተካከል የከተማ ግርግርና ጨዋታ እንጂ ፍፁም ድብርትና ድባቴ አይነበብም ነበር ። ሮሚናት አደባባይ በባጃጆች ረብሻ በቡቲኮች ስፒከር ሙዚቃ ደምቋል ።

ተጀምረው ያላለቁ ህንፃዎች ከማየት ወዲህ ጦርነቱን የሚያስታዉስ አንድም ነገር አላየንም ። በጋሪ ሙዝ ብርቱካን ፓፓያ የያዙ አዟሪዎች ሀውዜን አደባባይን አስጨንቀውታል ። የቦንዳ ልብሶችን ለመግዛት ወጣቶቹን መኪናውን ከበው ቆመዋል ። አፄ ዩሀንስ አደባባይን ዞረን ወደ ማረፊያችን ስናቀና ሰአቱ 10:20 ሆኖ ነበር ።

መቀሌ ከተማ 9 ዋና መስጂዶች እና ሁለት ትንንሽ መስጂዶች አሏት ። ከእነዚህ መሳጂዶች ውስጥ መስጂድ አል ራህማን በትግል የተሰራ የጠንካራ ትግራዋይ ሙስሊሞች መሰባሰቢያ ትልቅ መድረሳ አለው ማዕከል ሆኖ አገኘተነዋል ። እኛ ስንደርስ ትልልቅ ሰዎች የአካባቢው ሽማግሌዎች የመግሪብ ሰአት አዋርድ እያሉ ነበር ።

የመግሪብ ሶላታችንን ሰግደን ስናጠናቅቅ ወደ ማረፊያችን በመሄድ ከኡሙ አይመን ጀመአ አመራሮች ጋር ሹራ ለማድረግ ተቀመጥን ። እኛ ከመነሳታችን አስቀድመን በጭነት መኪና የላክናቸው ቁርአኖች ወደ 6 ሺ የሚጠጉ በመሆናቸው ከመቀሌ ከተማ ወጣ ብለው የሚገኙና ገጠራማ ቦታዎች ውስጥ ያሉ መድረሳዎች ብዛታቸውን እንዲሁም የደረሶቻቸውን መጠን የመለየት ስራ ሰርተን ሹራው ከተጠናቀቀ በኋላ ለጠዋት ቀጠሮ ይዘን ወደ መኝታችን አቀናን ።

ከፈጅር ሶላት በኋላ የመጀመሪያ መዳረሻችን ወደሆነችው አዲ ጉደም ገጠራማ ስፍራ ወደሚገኙ መድረሳዎች ቁርአኖችን ሸክፈን አቀናን ። ከመቀሌ ከተማ ትንሽ ወጣ እንዳልን ነበር መንገዶቹ ሁሉ የጦርነት ጠባሳ ያረፈባቸው እንደሆኑ ማስተዋል የጀመርነው ። በጅምር የቀሩ የመንገድ ዳር ህንፃዎች በፍርስራሽ ተሞልተው መመልከት ያስደነግጣል ። አፍላ ወጣቶች በመሮጫ እድሜያቸው ክራንችን ተመርኩዘው ሲራመዱ ማየት ልብ ያደማል ። የአዛውንቶች ፊት ላይ የሚነበብ ሀዘን ለጉድ ነው ። ወጣቶቹ ስላለፉበት አሰቃቂ የጦር ግንባሮች እያወጉን አዲ ጉደም ገጠራማ መድረሳዎች ደረስን ።

እግራችን ከመኪና እንደወረደ በመቶዎች የሚቆጠሩ ህፃናት በተክቢራ የመርጂዱን ቅጥር ግቢ ያሞቆት ጀመር ። እኛም ከሀዘን ስሜት ወጥተን በደስታ የናፈቁን ደረሶችን መዘየር ተያያዝን ። በኡስታዞቻቸው መሪነት በትግረኛ ቋንቋ ያዘጋጁትን ነሺዳ ሲያቀርቡ መመልከት አንጀት የሚበላ ስሜት ነበረው ።

አፍታም ሳይቆይ እኒያ ለአይን የሚያሳሱ የትግራይ እናቶችን ሀዘናቸውን በልባቸው አምባሻና ምግብ በጀርባቸው እንዳዘሉ ወደ መስጂዱ ሲገቡ ተመለከትን ። ታዲያ ቁርአን ይዞ የመጣ እንግዳ ክብር ይገባዋል ሲሉ እፊታችን ቆመው እንኳን ደህና መጣችሁልን እናንተ የሰላም መገለጫ የአማኝ መመሪያ የሆነውን ቅዱስ ቁርአን ለልጆቻችን ይዛችሁ መጣችሁ ታዲያ እኛ አቅማችን ቢደክም ግዜ ለማፍጠሪ የሚሆናችሁ ምግብ ብቻ ይዘን ነውና የመጣነው ይቅር በሉን በማለት ስሜታቸውን ገለፁ።

ይህ ነው የእስልምና እምነት ጠንካራ ገመድ ። በዘር አንገናኝም! በጎሳ አንድ አንድ አይደለንም ። በባህል አንዛመድም ። ይሄ ሁሉ ግን ለኛ ሙስሊሞች ተራ ነው ። ምክንያቱም ከዘር በላይ የጠበቀ ከባህል በላይ የረቀቀ አንድ ዘልአለማዊ መንገድ አገናኝቶናል ። አልሐምዱሊላህ ። ይህ ነው የኑር ቁርአን ባንክ ሽልማት ። ታዳጊዎችን ከናፈቃቸው የአላህ ቃል ጋር አገናኘናቸው ። የእናንተን አደራ ለአዲሱ ትውልድ አስረከብን ። የእናቶችን እንባ የአባቶችን ሀዘን ተጋርተን በሶብር አፅናንተን ዳግም ቁርአን በፈለጉ ግዜ እንደምንልክላቸው ቃል ገብተን የአዲ ጉደም ጉዟችን በስኬት አጠናቀቅን ።






ቀጣይ መዳረሻችን ውቅሮ ከተማ ነበር ። ውቅሮ የብዙ ባለ ሳይክሎች ሀገር ። ጦርነት አዘገያት እንጂ በእድገቷ መቀሌን እየተገዳደረች የነበረች ታሪካዊ ከተማ ። የአየር ንብረቷ ሞቃት ነዋሪዎቿ የፅናት ተምሳሌት ናቸው ። ውቅሮ ከተማ እንደገባን ቀድሞ ወደ ጆሮአችን የገባው የጁምአ ኹጥባ ድምፅ ነበር ። ውቅሮ ውስጥ ከሚገኘው ታላቁ መስጂደል አንዋር ነበር ድምፁ ።

የመስጂዱ ስፋት የጀመአው ብዛት ልብ ያሞቃል ። እጥር ምጥን ያለ ኹጥባ ካደመጥን በኋላ የጁመአ ሰላታችንን ሰግደን ከመስጂዱ አመራሮችና ከአካባቢው አባቶች ጋር ሹራ ተቀመጥን ። በቆይታችን የተረዳነው የትግራይ ሙስሊም ለዘመናት የሚዘይራቸው ወንድም አጥተው በናፍቆት ገጠራማ መድረሰዎች ቁርኣን አጥተው በቁጭት ከማዘን ጋር በአንድ ቁርኣን አምስትና ስድስት ታዳጊዎች በፈረቃ እንደሚቀሩ በአፅኖት ነገሩን ። እኛም ለውቅሮ ገጠራማ መድረሰዎች የሚበቁ ቁርኣኖችን ለየ መድረሰ ኡስታዞች አስረክበን በቀጣይ ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ አብረናቸው እንደምንሆን ቃል በመግባት ሹራችን በአባቶች ዱአ ተቋጨ ።

አሁን ጉዟችን መዳረሻ ታሪካዊዉና ንጉስ ነጃሺን ጨምሮ የበርካታ ሶሃቦች ዶሪህ (ቀብር) ወደሚገኝበት ታላቁ መስጂድ ነጃሺ ነው ። ያ ለመኪና እንኳ የሚከብድ ግዙፍ ተራራን መውጣት ጀምረናል ። የመንገዱ ርዝመት የአየሩ ሙቀት ቢከብድም መዳረሻችን የናፍቆታችን ማስታገሻ የሀዘን ስሜታችን ማበሻ ወደሆነ ክብር ያለው ታላቅ ቦታ ነውና በአዲስ የንቃት ስሜት ጉዟችን ቀጥለናል ።

የፍትሐዊነት ተምሳሌት የስደተኛ ሶሀቦች ከላለ ፣ የእንግዳ ተቀባይነት ምሳሌ ሆኖ የኖረው ታላቁ ንጉሥ ነጃሺ መስጂድ ደረስን ። ከመኪና ወርደን ፊት ለፊት በተመለከትነው ነገር ተደናገጥን ። ያ የታታላቅ ሶሃቦች መካነ መቃብር ያለበት ስፍራ አንዱ የጦርነት ሰለባ ሆኖ አርፏል ። የመስጂዱ ሚራናዎች በከባድ መሳሪያ ተመተው ማየት እጅግ ያስደነግጣል ። ቅርሶች ተዘርፈው መስጂዱ ለአናነት ቀርቦ መመልከት ልብ ያደማል ። ኡዱ አድርገን ሶላታችንን ሰገድን ።

ከጥቂት እረፍት በኋላ የመስጂዱ ጠባቂዎች ቅጥሩን ካስጎበኙንና መካነ መቃብሩን ካዘየሩን በኋላ የተፈጠረውን ነገር በእንባ ተሞልተው ነገሩን ። የሆነው ሁሉ ሆኖ አልፏል ። የእኛ ድርሻ በሰላም ማባሸርና ይዘነው በመጣነው ቅዱስ ቃል ህመማቸውን ማከም ብቻ ነበር ። ነጃሺ መስጂድ አቅራቢያ ያሉ ቁጥራቸው ወደ 5 የሚጠጉ የገጠር መድረሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ያህል ቁርኣን በተወካዮቻቸው በአስቀሪ ኡስታዞቻቸው አማካኝነት አስረክበን የአባቶችን ዱአ በመቀበል ወደ መቀሌ ከተማ ተጓዝን ።

አሁን የመጣንበት አላማ ፈፅመናል ። የያዝናቸውን ቁርኣኖች አከፋፍለን ታዳጊ ደረሶችን ዘይረናል ። ለቀጣይ በሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮች ዙሪያ ሰፊ ምክክር የጉዟችን አጋሮች ከሆኑ የኡሙ አይመን ጀመአ ሃላፊዎች ጋር ተመካክረን ንጋቱን ወደ ትግራይ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ለመሄድና ለመዘየር በመወሰን ምሽቱን በማረፊያችን አሳለፍን ።

እንቅልፍ የለም ሀዘን ነው ። በተመለከትነው ነገር አዝነናል ። ምን ማድረግ እንችላለን ?! የሁላችንም አእምሮ ጥያቄ ነበር ። ለሊቱን ከተኛንበት ክፍል ነቅተን የጉዞ ልዑካኑ ለሹራ ተቀመጥን ። ምን ማድረግ አለብን ?! በትግራይ ዙሪያ ምን መስራት እንችላለን?! ከብዙ የሀሳብ ፍጭት በኋላ በአንድ ነገር ተስማምተን ሹራችንን ቋጨን ።

ጠዋቱን ከኡሙ አይመን ጀመአ ጋር በመሆን ወደ ትግራይ ክልል መጅሊስ ቢሮ አመራን ። እጅግ በሚያስደስት አቀባበል በክብር ተቀብለው አነጋገሩን ። እስልምና እንጂ ሌላ ያላገናኘን የአኼራ ወንድሞች ከጦርነቱ ማግስት ድፍረት የተሞላበት ጉዞ በማካሄድ ትግራይን ስለዘየራቹ የአላህን ቃል ስላመጣቹ በአላህ ስም እናመሰግናለን ብለው የእውቅና ሰርተፍኬት ሸለሙን ። እኛም ደስታችንን በመግለፅ ምሽቱን ስላካሄድነው ሹራ አወጋናቸው ። እነርሱም ሀሳቡን እጅግ በማድነቅ በመጅሊሱ በኩል ለሀሳቡ እውቅና ሰጥተው ኘሮጀክቱን በመቀበል አፀደቁልን ።

ያዚያ ጉዞ ፍሬ የዚያራው ውጤት በትግራይ ክልል በመቀሌ ከተማ በአይነቱ የተለየ ታላቅ የጎዳና ላይ ኢፍጣር እንድናዘጋጅ ረድቶናል ። አልሐምዱሊላህ ከመቀሌ ከተመለስን በኋላ የረመዳን ወር ሳይጠናቀቅ እቅዳችንን ለመፈፀም ተባባሪ አካላትን በመፈለግ ከኡሙ አይመን ጀመአ ከትግራይ ክልል መጅሊስና ከትግራይ ክልል ሴቶች ጀመአ ጋር በመተባበር በከተማው ታላቅ የጎዳና ላይ ኢፍጣር በማወጋጀት የትግራይን ሰላም መሆን በአደባባይ በማስመስከር ከዚያ ዕለት በኋላ በርካታ የበጎ አድራጎት ተቋሞች በክልሉ ዙሪያ ለተቸገሩ ወገኖች እርዳታ እንዲያቀርቡ በአላህ ፍቃድ ሰበብ መሆን ችለናል ። ይህ ከኑር ቁርኣን ባንክ የጉዞ ልዑክ ከማይረሳ የጉዞ ገጠመኞች አንዱ ነበር ።

ጉጂ የሰው ጎርፍ

ከ ሀሽም ሙዘይን

ከአዲስ አበባ ቁርኣን ለማድረስ ወደ ምዕራብ ኦሮሚያ ጉጂ ዞን የተደረገ ብርሃናማ ጉዞ ። ሊሌት 11:30 ገደማ ። የሱቢሂ ሶላታችንን ሰግደን የጉዞ ዱአ በማድረግ እነሆ 'ቢስሚላህ' መንገድ ጀምረናል ። 1200 የሚሆኑ የቁርኣን ቅጂዎችን ጭነናል ። ዋና አላማችን የቁርኣን እውቀት ለማግኘት ለሚናፍቁ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ማድረስ ነበር ። ስለ ጉጂ ዞን ከእኛ የተሻለ ዕውቀት ያለው የጉዞ አሚራችን ወንድም አባስ አንዳንድ ነገሮች እያጫወተን በቀላሉ የሚያዙ የኦሮሚኛ ቃላቶችን እያስለመደን ደስ የሚል ጉዞ ማድረጋችንን ቀጥለናል ። ከመኪናው መስኮት አዲስ አበባ ቀስ በቀስ እየራቀች ስትሄድ፣ የሀገራችን አረንጓዴ ተራራዎች እና ሰፊ ሜዳዎች መታየት ጀመሩ። መኪናው በጠመዝማዛ መንገድ ላይ ሲያልፍ፣ የኦሮሚያ ክልል ውብ እና ለምለም መሬት አየሩን የበለጠ ንፁህ እና መንፈስን የሚያድስ አደረገው።

ጉዞው በሰላም ቀጠለ። በመንገድ ላይ የሚያማምሩ ገጠሮችን፣ በግጦሽ መሬት ላይ ያሉ እንስሳትን፣ እና በየመንገዱ የሚያልፉ ሰዎች ፈገግታን ተመለከትን። ጉዞው ረጅም ቢሆንም፣ አዝካሮችና ሀዲሶችን ፣ ቀልዶች፣ እና የቁርኣን ንባቦች ጊዜው በፍጥነት እንዲያልፍ አድርገውታል። ከብዙ ሰዓታት ጉዞ በኋላ፣ ዋደራ ከተማ ደረስን።

የደረስንበት ሰአት ምሽት 1:00 ሰአት ገደማ ነበር ። አካባቢው ካለበት ጊዜያዊ የፀጥታና ደህንነት ችግር ምክንያት በዚያ ቀን ዋደራ ከተማ ለማደር የሚያስገድድ ነበር ። መኪናችንን አቁመን ከተማ ውስጥ ያለ መስጂድ ፍለጋ ጥቂት ተራመድን ። በቅርብ ርቀት ሚናራው ጎልቶ የሚታይ መንፈስ የሚያድስ ግዙፍ መስጂድ ተመለከትን ። የኢሻ ሶላታችንን እዚያው ሰግደን ከመስጂዱ ጀመአዎች ጋር ያማረ ምሽት በማሳለፍ አዳራችንን እዚያው የመስጂዱ ማረፊያ ክፍል አደረግን ።

ከሱብሂ ሶላት በኋላ ዋደራ ከተማን ለቀን የፀጥታ አካላት ከሚታጀቡ መኪኖች ጋር በመሆን ወደ ጉጃ ዞን ሀርቀሎ ከተማ ተጓዝን ። የሀርቀሎ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ሃላፊ እና የ መስጂድ ኮሚቴ አመራር ከሆኑ እንቁ ወንድሞች ጋር ተገናኘን ። በተኮላተፈ ጣፋጭ አንደበት 'እንኳን ደህና መጣችሁ' ያሉን የኦሮሚኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ከወንድሞች ጋር ትውውቅ በማድረግ ወንድም አባስ የጉዞ መዳረሻዎቻችንን በተመለከተ ከአመራሮች ጋር አጭር ሹራ በማድረግ በቅድሚያ ወደምንሄድበት የሀርቀሎ ከተማ ትልቅ መስጂድ ወደሆነው መስጂድ አመራን ።

የሰው ጎርፍ ገጠመን ። የህዝብ ማዕበል ተመለከትን ። በሺ የሚቆጠሩ ታዳጊ ደረሶች በመቶ የሚቆጠሩ ኡስታዞች ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ያዘጋጁልን ደማቅ በተክቢራ የተሞላ አቀባበል አንድም የደስታ ሁለትም የድንጋጤ ስሜት እንዲሰማን አደረገ ።

የሆነው እንዲያ ነበር እኛ ከመምጣታችን ቀደም ተብሎ በጉጂ ዞን በሀርቀሎ ከተማና አጎራባች የገጠር መንደር ውስጥ የሚኖሩ ለዘመናት ቁርአንን ጣውላ ላይ ተፅፎ እንጂ በጁዝ የተረደረ የቁርአን ኮፒ ማግኘት የከበዳቸው እልፍ ሙስሊሞች ቁርአን የሚያመጣላችሁ ድርጅት ሊመጣ ነው ተብሎ የተወራ ወሬ ሰምተው ከያሉበት የገጠር መንደር በኡስታዞቻቸው መሪነት በታላቅ ጉጉት ሀርቀሎ ከተማ የሚገኘውን መስጂድ ሞልተው የጠበቁን ።

የወንድሞቻችን እና እህቶቻችን በጉጉት ሲጠብቁን እንደነበረ ስንደርስ ባደረጉልን ደማቅ አቀባበል ተረዳን ። የደስታ ስሜታቸው ፊታቸው ላይ በግልጽ ይታይ ነበር ። ይህ ለቁርአን ጥልቅ ፍቅር ያለውን ማህበረሰብ መመልከት እጅግ ልብ የሚያሞቅ ብቻ ሳይሆን ቀጣዩ ትውልድ ላይ የበዛ ተስፋ የሚያስጥል አጋጣሚ ጭምር ነበር ። ዳሩ ግን እኛ ይዘነው የሄድነው ቁርአን ለኒያ ሁሉ ምስኪን ደረሶች የሚበቃ አልነበረም ። እንዲያውም ከግማሽ በታች ለሚሆኑት ብቻ የሚደርስ በመሆኑ ከባድ ጭንቀትና ሀዘን ተሰማን ።

ሸይኽ አዲሱ ገመዳ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ተወዳጅ ተደማጭ የሆኑ ኡስታዝ በመሆናቸው ቀረብ ብለን ምን ተሻለ ስንል ጭንቀታችንን አስረዳናቸው ። ኋላ ላይ ያመጣነው ቁርአን እጅግ ሩቅ ከሆኑ ገጠራማ አካባቢዎች ለመጡ ደረሶች ብቻ እንዲሰጥና ለቀሪዎቹ ግን የማፅናኛ ቃል በመጠቀም ልባችሁ እንዳይሰበር በቅርቡ ተጨማሪ ቁርአን አፈላልገን እንደምንመጣ ቃል እንድንገባ ተስማምተን ጉዳዩን አስረዳናቸው ።

ታዲያ ለጥቂቶችም ቢሆን የቁርአን ቅጂዎችን ከሰጠናቸው በኋላ ያደረጉት ምስጋና እና ዱዓ በጣም ልብ የሚነካ ነበር። ብዙዎቹ የቁርአን እውቀት ለመማር ምን ያህል እንደሚጓጉ ገልጸውልናል። አንዳንድ ሰዎች ቀደም ሲል ለብዙ አመታት ቁርአን ለማግኘት ሲጠብቁ እንደነበር ነግረውናል። ቀሪዎቹም እንኳን እናንተ መጣችሁልን ። አሁን ችግራችንን ቀርባችሁ ማየታችሁ ተስፋ ይሆነናል አብሽሩ አትጨነቁ ሲሉ ልባችንን አረጋጉት ።

ይህ ጉዞ ቁርአንን ለሌሎች የማድረስ አስፈላጊነትን ብቻ ሳይሆን፣ ኢስላማዊ ወንድማማችነትን እና የእውቀት ፍቅርን በሚያሳይ መልኩ ከፍ አድርጎ አሳይቶናል። በዛው ሰአት የገጠመንን ሁሉ የወዳጆቻችን ለማሳወቅ የማህበራዊ ሚዲያዎች የሚሰራጩ መልዕክቶችን በማስረጃ አስደግፈን አስተላለፍን ።

ያን ቀን በዛ መልኩ ታዳጊዎችን ሸኝተን ወደ ማረፊያችን ተጓዝን ። በነጋታው ከሀርቀሎ ወጣ ብላ ወደምትገኘው ነገሌ ቦረና ጎራ ብለን በአካባቢው ያሉ ደረሶችና ኡስታዞችን ዘይረን ለእነርሱም በቅርቡ ማህበረሰቡን በማስተባበር በቂ የቁርአን ኮፒዎችን ይዘን እንደምንመጣ ቃል ገብተን ወደ አዲስ አበባ ተመለስን ።





በርካታ የምስልና የቪድዮ መረጃዎችን በማህበራዊ ሚዲያዎች በማሰራጨት የኑር ቁርኣን ቤተሰቦች ለጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጡት የማድረግ ፣ በቲክቶክ የቀጥታ ስርጭት 'ጉጂ ትጣራለች' በሚል መሪ ቃል የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በመፍጠር በአላህ ፍቃድ በመላው አለም የኑር ቁርኣን ባንክ ቤተሰቦች ለጉጂ ዞን የሚዳረሱ ቁርኣኖችን እንዲገዙልን በማድረግ በአጭር ጊዜ ውስጥ የምንፈልገው ያህል የቁርኣን ኮፒዎችን በማግኘት በድጋሚ ወደነዚያ የቁርኣን ትውልዶች የዲን ዘቦች የዱንያ ችግርና መከራ ረሀብና አልባሳ ግድ ሳይሰጣቸው ትኩረታቸው አላህን ማወቅ ፍላጎታቸው እስልምናን መረዳት ወደሆኑት የጉጂ ወንድምና እህቶች ጋር ለማድረግ ተነሳን ።

ዳግማዊ ጉዟአችን በወንድም አባስና በሸይኽ አዲሱ አስተባባሪነት በጉጂ ዞን ሀርቀሎ ከተማ እና አጎራባች የገጠር መንደሮች በመጓዝ የገባነውን ቃል ለመፈፀም አላህ አበቃን ። ያኔ የተሰበረ ልባቸውን አሁን መጠገን ችለናል ። እኒያ እንጨት ላይ እየፃፉ ሲቀሩ የነበሩ ደረሶች በአላህ ችሮታ ዛሬ ቁርኣን አግኝተዋል ። ቀጥሎም ወደ ነገሌ ቦረና ተጉዘን የገባነውን ቃል ለመፈፀም ኡስታዞችና ደረሶችን ተገናኘን ። ባማረ አቀባበል በደመቀ ዝግጅት ይዘን የመጣነውን የቁርኣን ኮፒዎች አስረክበን ለእናንተ ለውድ ቤተሰቦቻችን የሚተርፍ ዱአ ሰንቀን በአላህ ፍቃድ ወደ አዲስ አበባ መመለስ ችለናል ። ይህ የሰው ጎርፍ ያየንበት የህዝብ ማዕበል የተመለከትንበት ልባችን በደስታ ተሞልቶ አላህ ይጠብቃችሁ ስንል ዛሬ ድረስ የምንመርቃቸው የጉጂ ህዝቦች የሚኖሩት ህይወት ነው







ሐመር ትላንትና ዛሬ

ከ ሀሸም ሙዘይን

ከአዲስ አበባ ተነስቶ ደቡብ ኢትዮጵያ በኦሞ ሸለቆ ለመጓዝ ማሰብ ብቻ ለየት ያለ ስሜት አለው ። ምክንያቱም እኒያ በባህላቸው የተለዩ ከከተማም ከገጠርም የአኗኗር ዘዬ ትንሽ ወጣ ያሉ የራሳቸው ቀለም ያላቸው ማህበረሰቦች ወደሚገኙበት ስፍራ ነውና የምንጓዘው ። የዚህ ጉዞ ዓላማ የእስልምናን ብርሃን የማዳረስ ተልዕኮ ያዘለ ነውና ገና ከመነሻው ደስታ ናፍቆትና ጉጉትን ያስከተለ ነው ።

ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ እየተጓዙ ሲሄዱ አረንጓዴው የኢትዮጵያ ደጋማ ቦታ ቀስ በቀስ ወደ ሞቃታማና ደረቅ ሜዳ ይለወጣል። ይህ አካባቢ ደግሞ የልዩ ልዩ ብሔር ብሔረሰቦች መኖሪያ ነው። ከመንገዶቹ በአንዱ ላይ፣ ወደ ሐመር ብሔረሰብ መገኛ፣ ወደ ደቡብ ኦሞ ዞን ደረስን።

ከመድረሳችን በፊት የመልክአ ምድሩ አቀማመጥ ይበልጥ ደረቅ እየሆነ መጣ። በመንገዱ ዳር የሚገኙት ዛፎች እና ቁጥቋጦዎች እየሳሱ ሲሄዱ፣ የሙቀቱ መጠን እየጨመረ መጣ። ከሰአታት ጉዞ በኋላ ወይጦ ከተማ ደረስን ።

ወይጦ ስንደርስ የተቀበለን ተወዳጁ የዘመን ጌጥ የደቡብ ኦሞ ጀግና የሐመሩ ብርቱ ወጣቱ ቢላል ማሚዶ ነበር ። ውድ አንባቢያን መቼም ኑር የቁርአን ባንክን የሚያውቅ ቤተሰብ ቢላል ማሚዶን አያውቀውም ለማለት ይቸግራል ። በታሪክ እንደምናውቀው ኢትዮጵያዊው ቢላል የመጀመሪያውን አዛን ለሙስሊሞች እንዳሰማው ሁሉ የሐመሩ ቢላልም በሐመር ታሪክ የመጀመሪያውን አዛን በማሰማት ለማህበረሰቡ እስልምናን ያስተዋወቀ በሺ የሚቆጠሩ ሰዎችን በዳዕዋ ያሰለመ ታሪከ ሰፊ ገድለ ብዙ ወጣት ነው ። ታዲያ የኛም የጉዞ አላማ ይህን ወጣት ለማበርታት ላሰለማቸው ወንድምና እህቶች ቁርኣን ለመስጠትና ቀሪ የአካባቢው ነዋሪዎችን ለመዘየርና እግረ መንገድም ቢላል ያስጀመረውን የዳዕዋ ሂደቱን ለማስቀጠል ያለመ ነበር ።

ከወንድም ቢላል ጋር የጉዞ ልዑኩ በሞቃቷ ወይጦ ከተማ ትንሽ እረፍት ወስዶ በጉዞ ላይ ውይይት ካደረገ በኋላ በቀጥታ የወይጦን አስፓልት ለቀን ወደ ዘገርማ በና ፀማይና ሐመር የሚወስደውን ፒስታ መንገድ ተያያዝነው ።

የሐመር ብሔረሰብ መኖሪያ ደረቅና ሞቃት ቢሆንም፣ ባልተለመደ መልኩ ማራኪ የሆነ የተፈጥሮ ገጽታ አለው። እዚያ በረሐ ውስጥ የደረቁ ትናንሽ ቁጥቋጦዎች በየቦታው ይታያሉ። የሐመር ብሔረሰብ ሰዎች የአኗኗር ዘይቤ ከሌሎች የሚለያቸው ነው። መለስተኛ የአካልና የፊት ገፅታ ያላቸው ሲሆን፣ ቁመታቸው ደግሞ የረዘመ ነው። ሐመር ውስጥ ሙሉ ልብስ የማይታወቅ ያህል አይለበስም ። የሐመር ሴቶች ከፀጉራቸውና ከሸክላ አፈር የተሰራ ልዩ የፀጉር አበጣጠር አላቸው። ይህ አበጣጠር 'ጎልያ' ተብሎ የሚጠራ ሲሆን፣ ወንዶች ደግሞ ለየት ያሉ የራስጌ ጌጣጌጦችን ያደርጋሉ። እንዲሁም፣ በሰውነታቸው ላይ የተለያዩ ምልክቶችን ይነቀሳሉ። እያንዳንዳቸው ምልክቶች የራሳቸው

የሆነ ትርጉም አላቸው። ይህ ጉዞ ትክክለኛ የኢትዮጵያን ምስል ለመረዳት የሚያስችል ወሳኝ ተሞክሮ እንደሆነ በማመን የጉዞ ልዑኩ ወደቀዳሚ መዳረሻ 'ዘገርማ' ቀበሌ ደርሰናል ።

አቀባበሉ የተለየ ነበር ። እስልምናን ከተዋወቁ ገና የወራት እድሜ ካላቸው ሰዎች ጋር ስንገናኝ አባቶች ከታዳጊ ልጆቻቸው ጋር በመሆን በሚኮላተፍ አንደበታቸው 'አላሁ አክበር' እያሉ ነበር አካባቢውን ያሞቁት ። ያመጣናቸውን ቁርኣኖች አስረክበን የናፈቁ ወንድሞችን ዘይረን ከነሱ አደራ ተቀበልን ። ይህ ማህበረሰብ ለእስልምና አዲስ እንደመሆኑ እውቀት የሚያስጨብጧቸው መምህሮች ፣ ማንነታቸውን በዲን ለመቅረጽ ሶላት የሚሰግዱበት መስጂድና ፣ ልጆቻቸውን የሚያስተምሩበት መድረሳ ከጥያቄዎቻቸው ውስጥ ጎልተው የተሰሙት ነበር ። ከመርቂቃ ቀበሌ ቀጥለን ዘገርማ ቀበሌ መጨረሻች ደግሞ በና ቀበሌ ነበር ።

በዚህ ሰፋ ያለ ጊዜ የወሰድንበት የዚያራ ኘሮግራም በሐመርና በና ፀማይ ማህበረሰብ የአኗኗር ባህልን ያየንበት ከመሆኑ ጋር የበረሐው ንዳድ የውሃ ጉድጓድ እንደሚያስፈልገው የተረዳንበት ነበር ። ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሯቸው ጥቂት አርብቶ አደሮች ቤተሰቦቻቸውን ለማኖር በሚተጉበት ርቀት ልክ እስልምናን ለመረዳት ይተጋሉ ።

በረሐው ሙቀትን ድርቁ ደግሞ ረሀብን አስከትሏል። በአይናችን የተመለከትነው ችግር ዘርፈ ብዙ ነበር ። በኛ አንድ ግዜ ጉዞ የሚቀረፍ አልነበረም ። ጀግናው ቢላል የተጋፈጠው ይህን ሁሉ ችግር ነበር ። የማህበረሰቡን የኑሮ ችግር ፣ የእውቀት ጥማት ፣ የአክፍሮት ሃላትን የበረታ በትር በአንድ ትከሻው ተሸክሞ ይጓዛል ለቀሪ ማህበረሰቦች ዳዕዋ ሊያደርግ ። ይህን ፅናት በጉዟችን ተመለከትን ። ቢላልና ጓደኞቹ አላህ ምንዳቸውን በዱንያም በአኼራም እንዲከፍላቸው ተማፅነናል ።

በሦስት ቀናት የዚያራ ኘሮግራም የተመለከትነውን ልብ የሚነካ ገጠመኝ ከሐመር ከተማ ወጣ ብለን በጂንካ ከተማ ማረፊያችን ተቀምጠን መከርንበት ። ምን ማድረግ አለብን ?! ከብዙ የሀሳብ ፍጭትና ጠንካራ ውይይት በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰን የጉዳዩን ክብደት ለኑር ቁርኣን ባንክ የዘወትር ደጋፊዎች በማስረዳት ለዚህ ምስኪን ማህበረሰብ አፋጣኝ እርዳታ ማድረስ እንዳለብን ተማምነን እንቅስቃሴ ማድረግ ጀምረናል ።

ሰውን ያላመረገነ አላህን አያመሰግንም ነውና ነገሩ እናንተ ቤተሰቦቻችንን ዛሬ ላይ በላቀ ክብር ስናመሰግናችሁ ሐመር ላይ በአላህ ፍቃድና በእናንተ እገዛ ደማቅ ታሪክ በመስራታችን ነው ። ውድ አንባቢያን የዛ ጉዞ መነሻ ነገሩን በቴሌቪዥን መስኮት ለመላው አለም ማስመልከት እንዳለብን ያሳመነ ነበርና ሚንበር ቴሌቪዥን በሰጠን እድል ተጠቅመን ስለ ሐመር ለአለም ተናገርን ። ብዙዎች ልባቸው ተነካ ። እልፎቹ አዘኑ ። እናም ለሐመር እኛ አለንላችሁ ብለው አበረቱን ። ከዚያ ጊዜ በኋላ ባደረግነው ተደጋጋሚ ጉዞ በበና ፀማይና ሐመር ወረዳ የተጀመሩ መስጂዶች እንዲያልቁ ፣ ምንጣፍ ሶላርና ስፒከር ተገጥሞ ለመጀመሪያ ጊዜ አዛን ጎልቶ እንዲሰማ ሰበብ ሆንን ። በዚህ አላበቃም የኑር ቁርኣን ባንክ የጉዞ ልዑክ አስቸኳይ የምግብ እርዳታ መርሐግብር ተዘጋጅቶ ሰለምቴ ወንድምና እህቶች በህይወታቸው የመጀመሪያ የሆነውን የረመዷን ፆም እንዲፆሙና ሳይቸገሩ እንዲያፈጥሩ የእህል ድጋፍ ፣ በርካታ የአልባሳትና ቁሳቁስ ድጋፍ እንዲደረግ ምክንያት ሆነናል ።

በዚህ አላበቃም ከረመዳን ፆም በኋላ የመጀመሪያ ኢዳቸውን ከሚያከብሩ ተናፋቂ የሐመር ወንድሞች ጋር የኢድ ሶላት በጋራ በመስገድ ከተባባሪ አካላት ጋር የዑዱሁያ ስነስርአት በማከናወን ከ40 በላይ በሬዎች ታርደው ያማረ ኢድ በጋራ አሳልፈናል ። ታዲያ ለኒህ ምስኪኖች ጊዜና ዕውቀታቸውን ሰውተው የሚያስተምሩ ኡስታዞችን በመቅጠር በዘላቂነት ቁርኣን እንዲቀሩና የእስልምና ትምህር እንዲማሩ ተደርጓል ። ለዚህም ያግዝ ዘንድ ከተባባሪ አካላት ጋር በመሆን በበና ፀማይና ሐመር ወረዳ ሁለት ዘመናዊ ወፍጮ ቤቶችን ገንብተን የወፍጮ ማሽኑን በመትከል አንድም ለዘመናት በእጃቸው ሲፈጩ የተጎዱ እናትና እህቶቻችንን እረፍት በመስጠት ተጨማሪ ለኡስታዞች ደሞዝ የሚከፍል ተቋም ገንብተናል ። ውድ አንባቢያን ባለፉት አመታት ውስጥ በሐመርና በና ፀማይ ውስጥ ይሄ ሁሉ ስራ ሲከወን በብዙ ገጠመኞችና በእልፍ ስንክ ሳሮች የተሞሉ መሆናቸውን ልብ ይሏል ። የአላህ ፈቃድ ሆኖ አለፈ እንጂ ተደጋጋሚ ተንኮልና ሴራዎች ጠልፈው ሊጥሉን ሞክረዋል ። የእስር ገጠመኝን ጨምሮ በአላህ ፍቃድ የታለፉ አደጋዎች የበዙ ነበሩ ።



የጉዞ ማስታወሻ

يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِنَّا خَلَقْنَاكُم مِّن ذَكَرٍ
وَأُنثَىٰ وَجَعَلْنَاكُمْ شُعُوبًا وَقَبَائِلَ لِتَعَارَفُوا ۚ إِنَّ
أَكْرَمَكُمْ عِندَ اللَّهِ أَتْقَاكُمْ ۚ إِنَّ اللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٌ

እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ። እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ። አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው። አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነው።

ድንገት ከምትኖሩበት ቀዬ ከለመዳችሁት አየር ከለመዳችሁት ከባቢ ተነጥላችሁ ወደማታውቁት ስፍራ ለአንዳች የሕይወት ልምምድ ብታቀኑ አዕምሮአችሁ ውስጥ ጥያቄ፣ፍርሃት፣ደስታ፣ግርታ ዝብርቅርቅ ስሜት ይርመሰመሰል። የምሄድበት አዲሱ ስፍራ ምን ይሆን ይሆን? እዛ አካባቢ ያለው የአየር ጠባይ ሞቃታማ ነው ቀዝቃዛ የአካባቢው ማኅበረ-ሰው ምን ይመገባል ? ቋንቋቸውስ ምን አይነት ነው በምን እንግባባ ይሆን እያልን እንጠይቃለን።

ከአደም (ዐ.ሰ) ፍጥረት ተነስተን የሰው ልጅ በየጎሳው በየነገዱ በቀለም ልዩነቱና በአኗኗር ዘይቤው ጉራማይሌነትን ተላብሷል አላህ ይህን ፍጥረተ-ዓለም ሲዘረጋው ለሰው ልጅ ሕይወት እንዲመች አድርጎ ፈጥሮለታል። በአለም ላይ በግምት ከ 7000-8000 (ከሰባት ሺህ እስከ ስምንት ሺህ) ቋንቋዎች ይነገራሉ ቋንቋ እየተወለደ ይሞታልና የቁጥር ከፍ ዝቅን አጥንቶ ለማወቅም ይቸግራል ብለን ብናስብ ልሳናችን ከጥቂት ቋንቋዎች ውጭ የመናገር ክህሎቱ እጅግ ጥቂት ነው። አይደለም ከዓለም ሕዝብ ጋር በዚህ ሁሉ ቋንቋ ለመግባባት ቅርባችን ካለው ሁለትና ሶስት ልሳን ጋር መነጋገር ይከብደናል። ግን አይለመድ የለ ሰው ሆኖ ከሌላ ሰው ጋር በነፍስ ቋንቋ ለመነጋገር አላህ (ሱ.ወ) ሰውን በሰብዓዊነቱ ብቻ አልቆታል።የአካባቢው ማኅበረ-ሰው ምን ይመገባል ? ቋንቋቸውስ ምን አይነት ነው በምን እንግባባ ይሆን እያልን እንጠይቃለን።





ይህን የኑር ቁርአን ባንክ ኢስላማዊ ማኅበር አምስተኛ አመት አስመልክቶ ለሕትመት ያበቃነው ቅጽ 1 መጽሔታችንን የምታነቡ ኣንባቢያን ኑር ቁርአን ከተመሰረተ ግዜ አንስቶ ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ ትልቁ ኃላፊነት የሆነውን ብርሃን የማድረስ ጉዞው ከጀመረ እና እኔም የስራቸውን ትጋት አይቼ እንደ አባል ከተቀላቀልኩ ግዜ አንስቶ በጉዞ ገጠመኝ ያየሁትን ትዝታ ላካፍላችሁ ያሰናዳሁት ፅሁፍ ነው አብራችሁኝ ጥቂት ቆይታ እንድታደርጉ ግብዣዬ ነው።

እንደወትሮው ሁሉ የኑር ቁርአን ልዑክ ለጉዞ የሚያደርገው ዝግጅት ቀደም ብሎና የመስክ ጥናት ከማኪሃድ ነው ሚጀምረው ይሄ ከተከናወነ በኋላ ለጉዞ የሚያስፈልገውን ዝግጅት በኑር ቁርአን በኩል ይከናወናል። ከጉዟችን በፊት ከምስራቅ ባሌዋ ሰዌና የተዋወቅንበት ገጠመኝ የጉዞ ባልደረባዬ አባስ በያን እንዲህ ይተርክልናል:-

" ከሰዌናና አካባቢዋ የተውጣጡ የአገር ሽማግሌዎችና ታዋቂ ሰዎች በማኅበረሰቡ የገንዘብ መዋጮ ተደርጎላቸው ወደ አዲስ አበባ ተሳፍረው በየመስጅዶች ደጅ እየዞሩ ቁርአን ፍለጋ ይኪትኑ ነበር። ወደ ኑር ቀርአን ባንክ ቢሮ በጥቆማ መጥተው ቢሮው ውስጥ የተቀመጠውን ቁርአንና የኑር ቁርአንን ገጽታ አይተው እነሱ ካሉበት ችግር አንፃር ይሄ ለነሱ እንደ ተዓምር ነውና ቢሮውን በተክቢራ አቀለጡት ።ከኔ ጋር በአፋን ኦሮሞ ስለተግባባን አካባቢያቸው ላይ ስላለው ችግር አስረድተው ወደ ሰዌና ለመምጣት ቃል ገብተንላቸው ተሰነባበትን ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ደውለው የአካባቢው ማኅበረሰብ ቁርአን እንደሚመጣለት ቃል ገብተን ስለዘገየ እኛ ሽማግሌዎች ከሰው ጋር ለመኗኗር አፍረናል ብለው በሀዘኔታ ነገሩን ። እኛም ከኑር ቁርአን ቤተሰቦቻችን ቁርአን ማሰባሰባችንን በርትተን ቀጠልን ከብዙ ትጋትና መጠበቅ በኋላ የሚቀሩበት ሉህ በሙስሐፍ ሊቀየር የብርሃን ጉዞ ቀጠሮ ተቆረጠ።"

ጉዞአችን የጀመረውን ከሌሊቱ 10:00 ሲሆን ሁላችንም በግዜ ለመሰባሰብ እንዲመችን በአንድ ቦታ ላይ አዳራችንን አደረግን መነሻችን አዲስ አበባ ነበር በሌት ስንነቃ ለጉዞ የሚያስፈልገንን ስንቅ እና ትጥቅ ሸክፈን ወደ መኪናችን አመራን ከመነሻውም የያዝነው የብርሃን ኃያል ነውና እግራችን ለጉዞ ሲንቀሳቀስ የብርሃን ጉዞውን እንዲያግዘን ዚክር በማድረግ ወደ አዳማ የፈጣን መንገድ መንገድ መግቢያ አቀናን። የጠዋት ጀንበር ልታዘቀዝቅ የሱብሂ አዛን ጥሪ ባይስተጋባም ሰዓታችንን አይተን ፈጣን መንገዱ አጋማሽ ላይ የሱብሂ ሰላታችንን ሰገድን።

ጉዞ ወደ ቢሾፍቱ፣አዳማ ፣ አሰላ እነዚህን መንገዶች ከፊታችን ላለው አድካሚ መንገድ ስንቅ እንዲሆነን ከሹፌራችን ውጭ ሁላችንም መኪናው ውስጥ ጋደም ብለን ምናሳልፍበት ሰዓት ነው በየመኋሉ እንቅልፍ ይላሸለበው ሰው ቀልድና ጨዋታ እየተዝናናን የጠዋቱን ፀሐይ በስሱ እየቀመስን እናልፋለን። እኔ ለዚህ ጉዞ እንግዳ በመሆኔ በየደረስኩበት ስለመንገዱና ስለ አካባቢው ሹፌራችንን መጠየቅ አልደክምም ትሁቱ ሹፌራችን ሙሐመድም መላው ኢትዮጵያን በጉዞ ስላዳረሰ በየደረስንበት ስላለፈው የጉዞ ትዝታ አካፍሎኛል ።

የጉዟችን መዳረሻ የምስራቋ አበባ የተፈጥሮና የውበት መናገሻ የሆነችው የኦሮሚያዋ ባሌ ናት ። ስለ ባሌ እኔ እንግዳው ብተርክ አይደንቅም ይልቅስ ባሌን በእንግዳ እግር የረገጣት ሳይሆን ተፈጥሮዋን እያጣጣመ የሚኖር የሀገሬው ሰውም እየተደነቀ የሚኖርባት ታሪኳ የማይዘለቅ ምድር ናት። የማለዳውን ንፋስ ከመኪናችን መስኮት እየሾለከ ቢያገኘን እንኳ ለነፍስም ለስጋም የሚያስቀይም አይደለም ። ይልቅስ በመስኮቱ በየመኋሉ አጮልቄ ከማየው ተፈጥሮ ጋር እያዋደድኩት የፍርሃት ፣ የግርታ፣ የዝብርቅርቅ መንፈሴ ተገፎ በተድላ እየተቀየረ ይመስላል ። ቁርስ ከረፈደ በቆጂ ደርሰናል ለቁርስ የሚስማማ ጥቂት ምግብ አንጀታችን ላይ አደረገን ። የበቆጂን እርጎ የጠጣ አየሩን የማገ ሰው እንዴ ከዚህ ሀገር ሀገሩን በክብር ሜዳል የሚያስጠራ አትሌት ካልፈለቀ ታዲያ ምኑን የበቆጂ ሰው አልሆነ ያስብላል። ጥሎብኝ እርጎ እወዳለሁ ይሄን ጣዕም ግን የትም አልደግመውም እያልኩ ሳጉረመርም ለሌላ ብዙ ግርምት ዳግም እግሬን ወደ ባሌ ምድር አነሳሁ።

የመልክዓምድሩ አቀማመጥ ያለመታከት በትንግርት መስኮት እያጮለቁ የሚያዩት ነው ። የተጓዝንበት ወቅ የአየር ጠባዩ የክረምት ነበር የሀገሬው ሰው ሰብሉን በየሜዳው ዘርግቶ ላየው ለተመለከተው ፈረንጅ ለቅንጦት ከርክሞ ያነጠፈው ሳር ይመስላል ። ኢትዮጵያ የብዙ ተፈጥሮ ሀብት እሴት ፣ባህል፣ወግ ማፍለቂያ ሀገር መሆኗን ወደ ባሌ የተጓዘ ይመሰክራል አንደኛው ምስክር እኔ ሆኜ በዚህ ድንቅ አጋጣሚ በመገኘቴ አላህን በእጅጉ አመሰገንኩት ።

ጉዞኣችንን ቀጥለናል መድረሻችን በአንድ ቀን ጉዞ የሚያልቅ አይደለምና ወደ ማረፊያችን የገጠር ከተማ ፍለጋ ለመድረስ ብዙ መገስገስ ይጠበቅብናል ። የአስር ሰላት ሲቃረብ ባሌ ሮቤ ደርሰናል ባሌ ሮቤ ላይ ያሳለፍነውን የምሳ ወቅትና ዝሁርና አስራችንን አጠናቀን ቀድሞ የተላከ የቁርአን ኮፒ መኪናችን ላይ ጭነን ወደ ቅርብ ማደሪያችን ጋሰራ ገሰገስን ። የመንገዱ አስቸጋሪ መሆን የጭቃና የዝናቡ ትዕይትን ተደርቦ መንገዳችን የተስተጓጎለ ቢመስልም ጋሰራ ጀምበር አዘቅዝቃ ጨለማ ቦታውን ይዞ መድረሳችን አልቀረም አዳራችንም እዛው ሆነ። ረኸም ጉዞ ወገብ ያጎብጣል ግን በእንደዚህ አይነት ልዩ ትዕይንት መታጀብ ድካም ያስረሳልና የሌት እንቅልፋችን ጎን የማሳረፍ ያህል ነበር ። ለሌላ ትጋት በሱብሂ አዛን ተቀስቅሰን በማለዳ ጉዟችንን ወደ ሰዌና አቀናን። ቀድመን ካለፍነው መንገድ የጠና በወጣ ገባ ኮረብታ የታጀበ መንገዳችንን ማሳበር ያዝን ከጥቂት መንገድ በኋላ ቁርሳችንን ተመግበን መንገዳችንን ቀጠልን ። ዝናቡ እየጠና መጣ የሀገሬው ሰው በየቀዬው ለእርሻ ሲርመሰመስ ፣ከብቶቹን ለግጦሽ ሲያሰማራ ይታያል። በእንዲህ አይነት ኃይል ባጀበው ዝናብ ከተፈጥሮ ጋር ተዋዶ ለመኖር የሚደረግ ጥረት ታላቅ የሕይወት ትምህርት ሆነልኝ ። የዝናቡ ጉልበትና የመንገዱ አስቸጋሪነት መኪናችንን በዳዴ የመሄድ ያህል ጉዞዋን ገታው ጋሰራ፣ጊኒር ፣ በርበሬን እያለፍን ልባችንም እግራችንም ወደ ሰዌና አቀና።



እዚህ አካባቢ ለሰባት አመት ገዳማ ዝናብ አላገኝም ነበር ከኛ መሄድ ጋር የዝናቡ ራህመት ተገጣጠመልን ሰዌና ደረስን ፀጥ ያለ የተጋጋ ትንሽ የገጠር ከተማ ተፈጥሮ በብዙ ፀጋ የከበበችው ቀዬ ነው ሰዌና። እንግዶቻቸውን በጉጉት ይጠብቁ የነበሩ የሀገሬው ሰዎች ደጃፋቸው ድረስ ኑር ቁርኣን መጣላቸው ደስታቸው ፊታቸው ላይ ይነበባል ። አቅፈው ስመው ተቀበሉን ሻንጣችንን ፣ስንቃችንን፣ ጓዛችንን አባቶች እንደታናሽ ወንድም ታናሽ ወንድሞች ደግሞ እንደታላቅ አክብረው አስተናገዱን ።

ሰዌና ጎናችን ያረፈው ሸህ ኸድር ቤት ነበር እርሳቸው እንግዳ ለመቀበል ቀበቶኣቸውን አጥብቀው ሸርጉድ ከሚሉ የሀገሬው ሰው በእንግዳ አክባሪነታቸውና በትህትናቸው የሚመሰክርላቸው ናቸው ። እነዚህ የሀገር ሽማግሌዎች በሀገራቸው ባህል ወግ መሰረት ለእንግዳ አቀባበል ፍየል እንዲታረድ ሸህ ከድር ጋር ስጦታ ይዘው መጡ መረቁን እንደልጆቻችን ነው ምንቆጥራችሁ አሉን ይዛችሁ የመጣችሁት ብርሃን ሰዌና ላይ አብርቷል አሉን ። የሄድነው የባዳ ቤት ወይን የማናውቀው ሀገር አይመስልም በቋንቋ ማልግባባቸው ሰዎች በፈገግታቸው ስደሳ በቋንቋቸው ሳይሆን አላህ የሰውን ልጅ እንዲግባባ በፈጠረበት የነፍስ ቋንቋ ተግባባን።

شُعُوبًا وَقَبَائِلَ لِتَعَارَفُوا ۚ إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِندَ اللَّهِ أَتْقَاكُمْ ۚ إِنَّ اللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٌ

እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ። እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ። አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው። አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነው።

እውነት ነው አላህ የመልክንና የቋንቋ ጉራማይሌነትን የፈጠረው የሰው ልጅ በነፍሱ ቋንቋ እንዲግባባ ነው ። ጎናችን እንዳረፈ የምሽት ወግ ተጀመረ ስለ አካባቢው ሰው ስለ መድረሳዎቻቸው ፣ ስለ ቂርኣት ፣ ስለ ደረሳዎቻቸው ብዙ ተነገረን ። ለዲን ያላቸው ፍላጎት ከነዛ ከመከራ የድርቅ አመታት እንኳን አንዳችን አልቀነሰባቸውም እኛ የእርዳታ እህል ሳይሆን እንድናመጣ የፈለጉት የአላህን ቃል ታያሉን ቁርኣን ነው እንድንሰጣቸው የፈለጉት ። ቴክኖሎጂ በነቃ ዘመን በሉህ እየፃፉ መሬት ላይ እየሰረዙ እየደለዙ እንደሚቀሩ መድረሳ አጥተው አውላላ ሜዳ ላይ በሀሩር እየነደዱ እንደሚቀሩ በጥልቅ ስሜት ነገሩን ። ህመማቸው ተጋባብን ።

ሕልም የነበረው መስጅድ እውን ሆነ

ሰዌና የገጠር ከተማ እና ዙሪያዋ ያሉ የማኅበረሰቡን ችግር ስናጠና መስክ ጉብኝት ስናደርግ በየቀዬው እየዞርን በእጃችን የያዝነውን ቁርኣን ስናደርስ እዚህ በፅሑፍ ተርኬ ማልዘልቀው ብዙ ሀመሞችን አየን ። በዚያ ንዳዳማ በረሃ ከውሃ በላይ የዲን እውቀት የጠማቸው ነዋሪዎችን ስታዘብ የነፍስ ጥያቄዬ በኣንክሮ ቀርቷል ። አጎራባች ቀበሌዎችን ማየታችን በተያዘለት ቀነ ገደብ እየተዟዟርን እያየን የነዚህ አጎራባች ቀበሌዎች የንግድና የማህበረሰብ ማዕከል የሆነችው ሰዌና የብዙ ደረሳዎች መናገሻ ናት ። አውላላ ሜዳ ላይ ይቀሩ የነበሩ ተማሪዎች እኛን እንኳን ደህና መጣችሁ ለማለት ተሰናድተው ጠብቀውናል እኛም ወደ ስፍራው አመራን ። ልጅ ያዘሉ እናቶች ፣ ጉልበታቸው ያልጠና ህፃናት ድንገት ብቅ ብሎ ከዘነበው ዝናብና ብርድ ጋር ተጋፍጠው "አህለን ቢኩም" (እንኳን መጣችሁልን) እያሉ ዘመሩልን ። በእንባና በደስታ ፣በሀዘንና፣በቁጭት የሚናጥ ጥልቅ ስሜት ሁላችንም ተጋባብን ። እዛው የሚረግፈው ዝናብ ላይ ቆመን ዝግጅቱን ለማከናወን ተገደድን በእጃችን የያዝነውን ቁርኣን አደልናቸው ደስታቸውም ፊታቸው ላይ ይነበብ ነበር።

አንድ የቀረ እና የሁላችንንም ልብ የሰበረ ነገር ከዚህ ዝብርቅርቅ ስሜት ጀርባ ነበር። ከቆምንበት ሜዳ ሁለት መቶ ሜትር ራቅ ብሎ በሕልም ዲዛይን የተደረገ በእውን የሚሰገድበት መስጅድ ተማሪዎች አግድም ጥለው በጭቃና አቧራ ሚቀሩበት መድረሳ አለ። እሱን እንድንጎበኝ ጋበዙን ። ልባችንን የተሰማው ስሜት በቃላት የሚገለፅ አይደለም ። እዚህ ከተማ መሃል በቅንጡ መስጅድ ግንባታ ስንሻኮት ለካ መሬት ላይ ተደፍቶም አላህን ሚገዛ አለ አልን ። የኢማሙ መቆሚያ እንደሚህራብ ምልክት በተደረጉ እንጨቶች ምልክት ተደርጎበታል። ከዚያ ውጭ ጣሪያም ግድግዳም የሌለው መስጅድ በሕልማቸው አቁመው አላህን ይገዛሉ።

አልሃምዱሊላህ ሕልም የነበረው መስጅድ እውን ሆነ ኑር ቁርኣን ባንክ ወደ ምስራቅ ባሌ ሰዌና ሲያቀና ያየውን የታዘበውን ለኑር ቁርኣን ቤተሰቦች ሀመሙን አስተላለፈ ። ልባቸው ለመልካም ስራ በር የተከፈተ ሶስት ወንድሞች ይህን የህልም መስጅድ እውን አደረጉት ። አውላላ ሜዳ ላይ ይቀሩ የነበሩ ደረሳዎችም ወደ መድረሳ ተሰበሰቡ ። ውድ አንባቢያን ይህ የሆነውን በሁለተኛ ዙር ጉዟችን ነው ። የጉዞ ትረካዬም ከብዙ ትዝብቶች በጥቂቱ የተቀነጨበ እንደመሆኑ ብዙ ያልተነገሩ ታሪኮች አሉት ። በብርሃን ጉዟችን ውስጥ ያለው የስሜት ከፍና ዝቅ በዚህ ማስታወሻ እንዳጋራኋችሁ ተስፋ አደርጋለሁ ።



NUR QURAN BANK ISLAMIC ASSOCIATION

+251929591670
+251911285537

በሞቶ ብር መስጀድ እንገንባ

ቁርጎን ለሁሉም

ቤንሻንጉል ጉምዝ

አንድ ቁርጎን ለአንድ ደረሳ

ጋምቤላ

ደቡብ

ጉዞ ብርሃን ይዞ

ትግራይ

አማራ

አፋር

ድርይዳዋ

አዲስ አበባ

ሀረር

አሮሚያ

ሶማሊያ

አንድ ቁርጎን ለአንድ ደረሳ

ጉዞ ብርሃን ይዞ

ቁርጎን ለሁሉም

በሞቶ ብር መስጀድ እንገንባ

7114

ለሁሉም ባንክ አጭር ኮድ

1000402052434 ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

0020949710301 ዘምዘም ባንክ

0143811100904100 አዋሽ ባንክ

1559758700001 ኦሮሚያ ባንክ

178179616 አቢሲኒያ ባንክ

1000071140001 ሂጅራ ባንክ